ዜና ሕይወቱ ወተጋድሎቱ



ለአቡነ ኢየሱስ ሞአ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ዜና ሕይወቱ ወተጋድሎቱ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዐ

አዘጋጅ፡- ሐይቅ ቅዱስ
አስጢፋኖስ አቡነ

ኢየሱስ ሞዐ አንድነት
ገዳም

2011 ዓ.ም.

Scanned by DocumentScanner | Lufick

© የአሳታሚው መብት
በሕግ የተጠበቀ ነው::

All Rights
Resrved

የመጀመርያ ዕትም 2003 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም 2006 ዓ.ም
ሦስተኛ ዕትም 2010 ዓ.ም
አራተኛ ዕትም 2011 ዓ.ም

☎ 0914-05-73-87
033-119 02 86

ማውጫ

መቅድም.....1
ምዕራፍ አንድ
የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ልደትና ዕድገት.....8
ምዕራፍ ሁለት
የምናኔ ሕይወት በደብረ ዳሞ ገዳም.....9
ምዕራፍ ሦስት
የሐይቅ ደብረ ነጎድጓድ ቅ/እስጢፋኖስ ገዳም መመሥረት እና የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ወደ ሐይቅ ደሴት መምጣት 17
ምዕራፍ አራት
የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ መምጣት 41
ምዕራፍ አምስት
የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ እረፍት....58

Scanned by DocumentScanner | Lufick

በዘመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

መቅድም

፩.፩ የገዳማዊ ሕይወት አደጋገር ጥንተ ነገር

ገዳማዊ ሕይወት ማለት በሙሉ ጊዜና ሕይወት እግዚአብሔርን ለማገልገል ቤተሰብንና ዘመድን፣ ሀብትና ንብረትን እንዲሁም በዚህ ዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር ትቶ በገዳም ተወስኖ መኖር ማለት ነው። በገዳም በተመሳሳይ ዓላማና ሕይወት በአንድነት የሚኖሩ «ማኅበረ መነኮሳት» ይባላሉ። ደጉም ቡዙኀር ሲረዱና ሲያሸግሉ ኑሯቸው በንፁህ ከሰው ተለይተው ቦታ ወስነው ብቻቸውን የሚኖሩት ባሕታውያን ይባላሉ።

ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን ዘመን በቤተሰብነታቸው የሚኖሩ እንደ መልከ ጼዴቅ፣ ኤልያስና ኤልሳዕ ያሉ አንዳንድ ቅዱሳን ነበሩ። ሔኖክም በዚህ ዓለም ተወሰ ይዘ ልጆችን ወልዶ መኖር ከጀመረ በኋላ ይህ አኗኗር ለመንፈሳዊ ፍላጎቱ አጥጋቢ ሆኖ ስላላገኘው የብሕትውና ኑሮ ጀምሯል፣ ከዚያም እግዚአብሔር ሰውሮታል።ዘፍ፭፡፳፬። ምንም እንኳ ብሕትውና ቀድም ብሎ ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም ምንኩስና ግን በሐዲስ ኪዳን ዘመን የተጀመረ የመንፈሳዊ ሕይወት መሃንድ ነው።

ለገዳማዊ ሕይወት፣ ለምንኩስናና ብሕትውና ጀማሪውና መሪው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይኸውም እንደተጠመቀ ወዲያውኑ ሳይውል ሳያድር ወደ ምድረ በዳ ሄዶ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ምንም ነገር ሳይቀምስ በተባሕትዎ በጸም ቆይቷል። በዚህም ለባሕታውያን ብሕትውናን ባርከና ቀድሶ ሰጥቷል። እንዲሁም በድንግልና በመኖር ለደናግልና ለመነኰሳት አብነትና መምህር ሆኗል። ማቴ ፬÷፩ ።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ ካደረበት የሚያድሩና ከዋለበት የሚውሉ ከእርሱ የማይለዩ ትምህርትና ተአምራት የማያከፈልባቸው መቶ ሃያ ቤተሰብ በመባል የሚጠሩ ነበሩ። እነዚህም አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፣ ሰባ ሁለቱ አርድእት እና ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ናቸው። እንዲሁም የክርስትና ሕይወት ሊጀመር አንዲት ልብና አንዲት አሳብ የነበራቸው ስምንት ሺህ ማኅበረ እስጢፋኖስ ነበሩ። እነዚህም ያላቸውን ነገር ሁሉ እያመጡ ከሐዋርያት እግር ስር እየጣሉ «ይህ የእንተ ነው፣ ይህ የእኔ ነው» ሳይባባሉ በአንድነት ለጸሎትና ለትምህርተ መንገል ጽሙዳን ሆነው ይኖሩ ነበር። ይህ ያላቸውን ሁሉ ትተው ከሐዋርያት አንድነት ገብተው መኖራቸው በመንኖ ጥሪት በአንድነት

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ለሚኖሩ ገዳማውያን መዘኻት አብነትና መሠረት ነው። የሐዋ.፱÷፴፪-፴፮።

በዘመነ ሐዋርያት ብዙ ክርስቲያኖች የወንጌልን ቃል ለመፈጸም ራሳቸውን ከማንኛውም ምድራዊ ተድላና ደስታ አርቀው በትህርምትና በብሕትውና ይኖሩ ነበር። በሁለተኛው መቶ ዓመት ክርስቲያን ደናግል በትዳሌና በበዓላት ሥርዓት ጊዜ ካህናትን ተከትለው ይታዩ ነበር። ከዚህም ከሁለተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ ብዙ ደናግል በእስክንድርያና በብዙ የክርስቲያን ሀገሮችና ቦታዎች ይታዩ ነበር። በየዘመኑ የነበሩ ቅዱሳን ሊቃውንትም በሚጽፏቸው መጻሕፍቶቻቸው የድንግልና ሕይወት አንዱና ዋና ርእሰ ጉዳያቸው ነበር። ደናግላን ሴቶች ብዙዎቹ በአንድነት እየተረዳዱ ይኖሩ ነበር። ወንዶች ደናግል ደግሞ ብዙዎቹ ከከተማቸውና ከመንደራቸው ወጣ ብለው በትንሽ ጎጆ ውስጥ ይኖሩ ነበር።

በዘመነ ሰማዕታት የተመሰረኑ ክርስቲያኖች ከሀገራቸው መሠደዳቸው መከራውን ለመሸሽ ወደ በረሃ ይሄዱ ነበር። የክርስቲያኖች ስደትና መከራ ሲያበቃ ብዙዎቹ ወደ ነበሩበት የዚህ ዓለም ሕይወት መመለስን ትተው በዚያው በጀመሩት

ገዳማዊ ሕይወት ዝናብ ቀጠለብኝ።ከዚህም ጋር ከዘመነ ሰማዕታት በኋላ በቤተ ክርስቲያን ላይ ይደርስ የነበረው የመከራ ዶፍ እና ስቃይ በማቆሙ ይልቁንም ለክርስትናው ሕይወት አዲስ ፈተና ሆኖ የመጣውን ቅምጥልነትን ዓለማዊነትና ምንፍቅናን ለመሸሽ ሲሉ ወደ ገዳማት ሄደው መኖርን የመረጡም ነበሩ። እነዚህ ምክንያቶች ለገዳማዊ ሕይወት መስፋፋት ታላቅ ሚና ነበራቸው።

በሐዲስ ኪዳን የምንኩስና ሕይወት ሥርዓት ባለው መልኩ የተጀመረው በቅዱስ እንጦንስ እና በቅዱስ ጳኩሚስ አማካይነት ነው። ቅዱስ እንጦንስ በ251 ዓ.ም በመካከለኛው ግብፅ ተወለደ። ቤተሰቦቹ ባለ ጸጋ የነበሩ ሲሆኑ እርሱ ግን ከሕፃንነቱ ጀምሮ ትዕግሥተኛና ሁል ጊዜ እናትና አባቱን እየተከተለ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄድና እንደ ሌሎች ልጆች ጨዋታ የማያታልለው ነበር። ከዚያም እናቱና አባቱ ሲሞቱ ብዙ ሀብትና ንብረት ትተውለት አልፈዋል። እርሱም ሳላቱን ምሳቱ በሐዋርያት ዘመን እንደ ነበረው ሀብትና ንብረትን ሁሉንም ነገር ትቶ ክርስቶስን ብቻ እያገለገለ መኖር ስለነበር ይህንን ቤተሰቡንም እያወጣና እያወረደ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስተዳደስ ሄደ። በትዳሴውም ሰዓት ካህኑ መንጌል ሲያነብ «ዓጽም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝሐብም በሰማያት ታገኛለህ፣

Scanned by DocumentScanner | Lufick

መጥተሀም ተከተለኝ» የሚለውን ሲያነብ ሰማ። ማቴ19፤21 በዚህ ጊዜ «እግዚአብሔር እኔን እንዲ ሲመክረኝ ነው»ብሎ ያለውን ሁሉ ሸጠ ለድሆች ሰጥቶ በትርብ ከሚገኝ ዋሻ ገብቶ በጸምና በጸሎት መኖር ጀመረ። ከዚያም ከነበረበት ዋሻ ወጥቶ ቡጣም ወደሚርቅ በረሃ ሄዶ ጽኑ ተጋድሎ ጀመረ። በእግዚአብሔር ኃያልም አጋንንትንና ፍትወታት እኩያትን ድል አደረገ።

ቅዱስ እንጦንስ ለሃያ ዓመታት ከበላቱ ሳያወጣ ዘግቶ በፍጹም ተባሕትዎ ከተጋደለ በኋላ ዜና ሕይወቱና ዝናው በዓለም እየተሰማ ሄደ። ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ እየመጡ እርሱን መስለው በምናኔ ሕይወት ፈጣሪያቸውን ማገልገል ጀመሩ።

ገዳማዊ ሕይወት በዚህ መልኩ ተጀምሮ በፍጥነት እየተስፋፋ ሄደ። በግብፅ ገዳማዊ ሕይወት ገዳማትን በመመሥረትና መነኮሳትን በመሰብሰብ ከፍተኛ ተጋድሎ የፈጸሙት ቀደምት አበው ከላይ እንደ ተገለጸው ቅዱስ እንጦንስ እና ቅዱስ ጳኩሚስ፣ ቅዱስ አሞንና፣ ቅዱስ መቃርዮስ ናቸው። አመሠራረቱና ዕድገቱም ባሏቸው እንደሚከተለው ነው።

ቅዱስ ጳኩሚስ (290-346) የመላእክት ኑሮ የሆነውን ገዳማዊ ሕይወት ለመኖር እየፈለጉ ነገር ግን ብቻቸውን በበረሃ ለመኖር ካለመቻላቸው የተነሣ ይህን ሕይወት መኖር ያልቻሉትን ሰዎች እያሰበ ስለ እነርሱ ያዝን ነበር። ከዕለታት በአንድ ወቅት በበረሃ ላለ መልአክ መጥቶ በነሐስ ሰሌዳ ላይ የተጻፈ ሕግ ሰጠውና እግዚአብሔርን በሙሉ ሕይወታቸው ሊያገለግሉ ወደ እርሱ የሚመጡትን በዚህ በሰጠው ሕግ መሠረት እንዲቀበላቸውና እንዲመራቸው ነገረው።

ገዳማትን በመመሥረትና መነኮሳትን በመሰብሰብ ከቅዱስ እንጦንስ ጋር ከፍተኛ ቦታ ያለው ይህ ቅዱስ ጳኩሚስ ነው። ከመልአኩ በተነገረው መሠረት በ320 ዓ.ም በዓባይ ወንዝ አጠገብ ከሚገኘው ዳውናስ (ታቤኒሲስ) በሚባል ቦታ ገዳም መሠረተ። በቅዱስ ጳኩሚስ ገዳም በጣም ብዙ መነኮሳትና ባሕታውያን ነበሩ። ቅዱስ ጳኩሚስ በሕይወት ላለ ዘጠኝ የወንድና ሁለት የሴት ገዳማትን መሥርቷል። የሴቶች ገዳማት እመምኔቷ የቅዱስ ጳኩሚስ እኅት ማርያም ነበረች። ቅዱስ ጳኩሚስ በ346 ዓ.ም. ሲያርፍ፣ ብዙ ገዳማት ተመሥርተው ተሥራፍተው እጅግ የበዛ መነኮሳትና ባሕታውያን በየገዳማቱ ይኖሩ ነበር። ዮሐንሳዊ የአንድነት ሕይወትን የጀመረው ይህ ታላቅ አባት ቅዱስ ጳኩሚስ ነው።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ቅዱስ ጳኮሚስ በላዕላይ ግብፅ ገዳማትን መሥርቶና አስፋፍቶ ካረፈ በኋላ ቅዱስ መቃርዮ ስደግሞ (330-390 ዓ.ም) በአስቄጥስ ገዳማዊ ሕይወትን አስፋፋ። ቅ/አንጦንስና ቅ/ጳኮሚስ ያረፉት ከቅ/መቃርዮስ በፊት ነው። ቅዱስ መቃርዮስ በአስቄጥስ በረሃ በብሕትውና ብዙ ጊዜ ከኖረ በኋላ አስቀድሞ ገና ለምናኔ ሲጠጣ ከአግዚአብሔር በተላከኪሩባዊ መልአክ እንደተነገረው ብዙ መናንያን መጥተውስለተሰባሰቡ አስቄጥስ በረሃ የባሕታውያንና የመነኰሳት መነሃርያ ሆነ።አስቄጥስ በረሃ ለግብፅ ገዳማት ዋና ማዕከል የሆነና እንደ አባ ብሶይ፣ ዮሐንስ ሐሊር፣ ሙሴ ጸሊም እና ሌሎችም ታላላቅ ቅዱሳን አባቶች የነበሩበት እና እንደ ሌሎቹ ገዳማት ብዙ ታላላቅ ቅዱሳን የተገኙበት ታላቅ ገዳም ነው።

ቅዱስ አሞን በቅዱስ እንጦንዮስ ዘመን የነበረ ሲሆን ከቅ/አንጦንስና ከቅ/ጳኮሚስ ቀጥሎ ገዳማትን የመሠረተና ያስፋፋ ቅዱስ አባት ነው።ቅዱስ አሞን ገዳም የመሠረተው በኒጥሪያ በረሃ ነው።እንደ ሌሎቹ ገዳማት ሁሉ በኒጥሪያም ብዙ መነኰሳትና ባሕታውያን ነበሩ። በዚህ ቦታ ከነበሩት ታላላቅ ቅዱሳንም እነ ቅዱስ መቃርዮስ ዘእስክንድርያ፣አባ

ወትሪስ (ኢቫግሪየስ) አባ ቴምድሮስ፣ አባ ኤስድሮስ ይገኙበታል።

በአጠቃላይ ገዳማትን የሚመሠርቱ አባቶችን በማፍራትና ሕይወቱን በማለማመድ እንዲሁም ሥርዓቱን በማስተማር ገዳማዊ ሕይወት በዓለም ሁሉ እንዲስፋፋ ዋና ማዕከል ሆነው ያገለገሉት በውስጣቸው በሚኖሩቅዱሳን እንደ አጥቢያ ኮከብ ያሸበረቁትና የደመቁትበግብፅ በረሃ የተመሠረቱት ገዳማት ናቸው።

ምንም እንኳ ገዳማዊ ሕይወት የተጀመረውና ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በግብፅ ቢሆንም በሶርያም ገዳማዊ ሕይወት በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቷል። በሶርያ ብዙ ታላላቅ ገዳማትና ገዳማውያን አባቶች ነበሩ። በተለይም ደግሞ በአንድ የድንጋይ ዓምድ ላይ ወጥተው ከዚያ ሳይወርዱ ለብዙ ጊዜ በዚያ ላይ ሆነው የሚጋደሉ «ዘዓምድ- ዓምደኞች» ባሕታውያን ነበሩ። የዚህ ዓይነቱ ተጋድሎ ሕይወት ጀማሪ ስምዖን ዘዓምድ ነው። ስምዖን ዘዓምድ በሶርያ በአንድ ዓምድ ላይ 40 ዓመት ኖሯል። እንዲሁም በሲና ተራራና በዮርዳኖስ በረሃ (ምድረ ፍልስጥዔም) ብዙ ባሕታውያን ይኖሩ ነበር። በቱስጥንጥንያና በታናሿ እስያም እንዲሁ ብዙ ገዳማትና መነኰሳት ነበሩ።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ለታናሿ እስያ ሥርዓተ ምንኩስና ዋናው አብነት የቀጰዶቅያው አባትታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ (330-379 ዓ.ም) ነው።

፩.፪ በሀገራችን በኢትዮጵያ የገዳማዊ ሕይወት አጀማመርና ዕድገት

ከሀያኛው የእስክንድርያ ፖትርያርክ ከታላቁ ከቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ጽጽስናን የተቀበለው የኢትዮጵያ ጳጳስ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ በግብጽ የነበረውን ገዳማዊ ሕይወት በተወሰነ ደረጃ ተመልክቶ እንደ መጣ ቢነገርም ገዳማዊ ሕይወት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በቅዱስ አባታችን በአቡነ አረጋዊ አማካይነት ነው። ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል አንዱ የሆነው አቡነ አረጋዊ ወደ ግብጽ ከቅዱስ ጳኩሚስ ገዳማት ሄዶ በቅዱስ ጳኩሚስ እግር ከተተኩት አበው መነኮሳት ሥርዓተ ገዳምን አጥንቶ ወደ ኢትዮጵያ መጣ። በርግጥ ሥርዓት ገዳም ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊትም ኢትዮጵያዊያን መናንያን በተለያዩ የግብፅ ገዳማት በምናኔ ይኖሩ ነበር። ከእነዚህም በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በተጋድሎው የሚታወቀውና በቅድስናው የሚከበረው ሙሴ ጸሊም ኢትዮጵያዊ እንደ ሆነ የሚታወቅ ነው።

አቡነ አረጋዊም ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላ ደብረ ዳሞ ገዳምን መሠረተ። በዚህ ሁኔታ ደብረ ዳሞ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳማዊ ሕያውት ዋና መሠረት ሆኖ ለብዙ ጊዜ ሲያገለግል ቆየ። ከደብረ ዳሞ በተጨማሪ ተሰዓቱ (9) ቅዱሳን የመሠረቷቸው ገዳማት ገዳማዊ ሕይወትን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ሆኖም ግን እስከ 13ኛው መቶ ዓመትድረስ ገዳማዊ ሕይወት ባብዛኛው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተወሰነ ነበር ለማለት ይቻላል።

በ13ኛው መቶ ዓመት በዚያው በደብረ ዳሞ በአባ ዮሐኒ እጅ የመነኰሰውና በገዳሙ ብዙ ዓመታት ሲያገለገል የነበረው አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ወደ ሐይቅ ቅ/ እስጢፋኖስ መጥቶ በዚያ ገዳም መሠረተ። ከደብረ ዳሞ ቀጥሎ ለገዳማዊ ሕይወት በኢትዮጵያ መስፋፋት ዋና ማዕከል ሆኖ ያገለገለው ይህ በአሥራ ሶስተኛው መቶ ዓመት በአቡነ ኢየሱስ ሞዐ የተመሠረተው የሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ነው።

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ቅዱሳን አማካይነት ገዳማዊ ሕይወት በአምስተኛው መቶ ዓመት ማለቂያ አካባቢ ተጀምሮ ከአሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት ወዲህ በጣም ተስፋፋ። ከአሥራ ሦስተኛው እስከ አሥራ አምስተኛው መቶ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ዓመት ማብቂያ ድረስ የነበረው ዘመን በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለገዳማዊ ሕይወት ወርቃማ ዘመን ነበር። የነገሥታቱና የመኳንንቱ ልጆች ሳይቀሩ እየመነኑ የሚገኙት በገዳማት ነበር።

የሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስን ገዳም የመሠረተው አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐም በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ያሉትን ታላላቅ ገዳማት የመሠረቱ ሌሎች ብዙ ቅዱሳን አባቶችን በማስተማርና በማመንኮስ በምንኩስና ወለደ። የሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም በዘመኑ ለሀገራቱም ሆነ ለቤተክርስቲያን ታላቅ የትምህርት ተቋም (ዩኒቨርሲቲ) ሆኖ አገለገለ። ከዚህ ገዳም መንፈሳዊ ሀይወትን ተላብሰው ተምረውና ተመርተው የወጡ አባቶች ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች በመሰማራት ገዳማትን መሠረቱ፣ ወንጌልን አስተማሩ ሰበኩ።

አቡነ ኢየሱስ ሞዐ በዚህ በሐይቅ ገዳም ካፈራቸው ታላላቅ አባቶች መካከልም የደብረ ሊባኖስን ገዳም የመሠረተው ታላቁ ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል (በዘመኑ ብዙ መነኮሳት የነበሩበትን ገዳም ከዛሬው ጋስጫ ገዳም ሥር የመሠረተና የብዙ መነኮሳት አባት የነበረ)፣ አቡነ ሂሩተ አምላክ (ዳጋ እስጢፋኖስን የመሠረተ)፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (ጋስጫ ገዳምን የመሠረተ)፣ አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ፣ አቡነ አሮን፣ አቡነ ገብረ ናዝራዊ፣ አቡነ ሕዝቅያስ እና ሌሎችም ይገኙበታል።

እነዚህ አባቶች በየሄዱበትና በየደረሱባቸው ቦታዎች ገዳማትን በመገደምና ወንጌልን በመስበክ ከፍተኛ ሐዋርያዊ ሥራ ፈጽመዋል። ከዚያ ቀጥሎም የእነርሱ ተተኪ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ተተኪዎችን እያፈሩና እያስማሩ ወንጌል በብዙ ቦታ እንዲሰበክና ክርስትና እንዲስፋፋ ከፍተኛ ተጋድሎ ፈጽመዋል። ወርቃማ ዘመን የተባለውን የመካከለኛውን ዘመን ወርቃማ ያሰኘው የእነዚህ አባቶች ድንቅ ሥራና ተጋድሎ ነበር። የዚህ የቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመን ምንጭና መሠረት ደግሞ በአባታችን በአቡነ ኢየሱስ ሞዐ የሐይቅ ቅ/እስጢፋኖስ ገዳማዊ ሕይወት መመሥረትና ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ይሰጥ የነበረው ትምህርትና ሐዋርያዊ ሥምሪት ነበር። ስለሆነም ታላቁ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳማዊ ሕይወትና ስብከተ ወንጌል ማበብና በዚያ በወርቃማው ዘመን ለደረሰበት ደረጃ ታላቅ ባለውለታ አባት ነው።

ይህ ገዳም በአሁኑ ጊዜ መልካም በሆነ ሁኔታ የተደራጀና የተለያዩ ሀብሀብ ሥራዎች እየተከናወኑበት ያለታላቅ ገዳም ነው። በገዳማዊ ሕይወትና በተግባረ ዕድ ይዘቱም ተስፋ ሰጭ ደረጃ ላይ ይገኛል። እግዚአብሔር ቢፈቅድ ገዳሙ ወደፊት ሊተገብራቸው ያሰባቸው የተለያዩ ፕሮጀክቶችም አሉ።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ምዕራፍ አንድ

የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ልደትና ዕድገት

በበጌምድር ግዛት (ሰሜን ጎንደር) ዳኅና ገብርኤል በሚባለው አጥቢያ ውስጥ ዘክርስቶስ እና እግዚእ ክብራ የተባሉ ደጋግ የሆኑ ባልና ሚስቶች ነበሩ። እነርሱም በእግዚአብሔር ዘንድ ቅዱሳን የሆኑና በዘመድም የከበሩ ነበሩ። ለልዑል እግዚአብሔር የሚገዙና እርሱን ጽሙዳን ሆነው የሚያገለግሉ፣ በሰዎችና በመላእክት ዘንድ ሞገስ የነበራቸውና በክርስትና ሃይማኖት ፍጹማን የሆኑ ጻድቃን ነበሩ።

እነርሱም ለእግዚአብሔር የሚገዛና ፈቃዱን የሚፈጽም መልካም የሆነና የተባረከ ልጅን ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔርን ዘወትር ይለምኑት ነበር። ይህንም ያደርግላቸው ዘንድ ለእግዚአብሔር ስእለት ተሳሉ። የጻድቃንና የሰማዕታትን የነቢያትንና የሐዋርያትን የሌሎች ቅዱሳንንም እንዲሁም የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን መታሰቢያ ያደርጉ ነበር፤ ይልቁንም ደግሞ ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና

ከሀሳ አስበልጣው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓል መታሰቢያ ያደርጉ ነበር። ልጅ እንዲሰጣቸው ይጸልዩና ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ በእኛ ላይ ይሁን ይሉ ነበር። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ጸሎታቸውንና ልመናቸውን ሰምቶ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ወደ እነርሱ ላከላቸው። መልአኩም ዘክርስቶስን «ጸሎትህ ወደ እግዚአብሔር ደረሰ፣ ልመናህም ወደ ሰማይ ዐረገ» አሰው። ሚስቱን እግዚእ ክብራንንም እንዲሁ «ልቅሶሽና ጩኸትሽ ቅድመ እግዚአብሔር ደረሰ፣ እግዚአብሔርም የልቡናሽን መሻት ፈጸመልሽ» አላት። ያም የእግዚአብሔር መልአክ ይህን ብሏቸው ወደ ሰማይ ዐረገ።

እግዚአብሔርም በመልአኩ ተስፋውን እንደ ነገራቸው ፈጸመላቸውና ሶስት ልጆችን ሰጣቸው። የአንዱ ስም ኢየሱስ ሞዐ፣ የሁለተኛው ስም ገብረ ጽዮን፣ የሦስተኛው ስም ደግሞ ስቡሐ አምላክ ይባላሉ። እነዚህም በሥራቸው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እየረዳቸው በመልካም አስተዳደግ አደጉ። የኢየሱስ ሞዐ ፅንሰቱ በነሐሴ ፳፮ (26) በ፲፩፻፺፭ (1195) ሰኞ ቀን ሲሆን ልደቱ ደግሞ ግንቦት ፳፮ (26) ረቡዕ በ፲፩፻፺፮ (1196) ዓ.ም በቅዱስ ነአኵቶ ለአብ ዘመነ መንግሥት ነው። አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ በወላጆቹ ቤት ጥበብን ሁሉ እየተማረና የብሉይ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን እየተመለከተ፣ በመልካም ሥነ ምግባርና በመንፈሳዊ ሕይወት መኖርን ገንዘብ እያደረገ አደገ። ዕለተ ሞቱን የዚህን ዓለም ጊዜያዊነትና ኃላፊነት እያሰበ ነፍሱን ይመክራትና ቀንና ሌሊትም ያለቅስ ነበር። እንደዚህ ባለ ሁኔታ በቅድስናና በንጽሕና ሕይወት በአባቱና በእናቱ ቤት ፴ (ሠላሳ) ዓመት ኖረ።

ምዕራፍ ሁለት

የምናኔ ሕይወት በደብረ ዳሞ ገዳም

ከዕለታት በአንድ ቀን የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ለአባታችን ለአቡነ ኢየሱስ ሞዐ በሌሊት ተገለጠለትና ሶስት ጊዜ ጠርቶ እንዲህ አለው፡- «ከአባትህ ቤት ውጣና የደብረ ዳሞ ገዳም መምህር ወደ ሆነው ወደ አባ ዮሐኒ ዘንድ ሂድ። በዚያም ለእግዚአብሔር ትገዛለህ፣ የግና የተባረክህ አገልጋይም ትሆናለህ።»

ከዚያ በኋላ አባቱና እናቱ ዘመዶቹም ተኝተው ሳለ ኢየሱስ ሞዐ ብቻውን ወጥቶ ሄደ። ገብርኤል ሚካኤል ከሚባል የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ካለበት ቦታ ደረሰ፣ በዚያም ሌሊቱን በመላ በተሰበረ መንፈስና በትሑት ልቡና ወደ እግዚአብሔር ሊጸልይና ሊማልድ አደረ።

በዚያም አንድ እግዚአብሔርን የሚፈራ ስሙ ይምጻእ ምህረት የሚባል አንድ ዲያቆን ነበረ። ይህ ዲያቆንም የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል በሌሊት ተገለጠለትና «ይምጻእ ምሕረት» «ይምጻእ ምሕረት» «ይምጻእ ምሕረት» ብሎ ጠራው። እንዲህ በጠራው ጊዜ ነቃና ተመልሶ ተኛ። ሁለተኛም እንደ ገና«ይምጻእ ምሕረት» «ይምጻእ ምሕረት» «ይምጻእ ምሕረት» ብሎ ጠራው«አንተ ማነህ?» ብሎ ጠየቀው። መልአኩም «እኔ ገብርኤል ነኝ» ብሎ መለሰለት። ያ ዲያቆንም «የሚናገረኝ ሰው ይሆን ወይስ መልአክ?» እያለ አሰበ። እንዲህ እያሰበ ላለ አሁንም እንደ ገና ለሦስተኛ ጊዜ «ይምጻእ ምሕረት» «ይምጻእ ምሕረት» «ይምጻእ ምሕረት» ብሎ ጠራው።

ይምጻእ ምሕረትም «እነሆኝ አለሁ» አለው። መልአኩም «እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፣ አሁንም ተነሥና ከአባትህ ቤት ወጥተህ በሩኩና ቅዱስ፣ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ ሞዐ ሂድ፤ መነከሴ ትሆን ዘንድ ከእርሱ ጋር አብረኸው ሂድ» አለው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐ በቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ ቁሞ ይጸልይና ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ይማልድ ነበር። የእግዚአብሔር መልአክ ገብርኤል ይህን ነገር በነገረው ጊዜ ያ ይምጻእ ምሕረት የተባለው ዲያቆን ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መጣ። በዚያም ብፁዕና ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው የሆነውን ኢየሱስ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ሞዐን ቆሞ ወደ እግዚአብሔር ሲማልድና ሲጸልይ አገኘው።

ከዚህ በኋላ ተገናኙና እርስ በርሳቸው እጅ ተነሳሱ፣ ሰላምታም ተሰጣጡ። የእግዚአብሔርን ገናናነትና ቸርነት እየተነጋገሩ፣ እንዲሁም በጸሎትና በልመና ሆነው መላዉ ን ሌሊት በቤተ ክርስቲያን አደሩ። በነጋም ጊዜ ከነበሩበት ቦታ ርቆ ወደሚገኝ ቦታ ተጓዙ፤ እግዚአብሔርን የሚፈራና ጻድቅ የሆነ አባ ዮሐኒ ወደሚኖርበት ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ደረሱ።

ወደ እርሱም በደረሱ ጊዜ ኢየሱስ ሞዐ አባ ዮሐኒን መንፈሳዊ በሆነ ሰላምታ ቡትህትና እጅ ሦሣው። እጅ በሦሣው ጊዜም ቅዱስ አባ ዮሐኒ መረመረው፤ «ልጄ ሆይ ወደዚህ ለምን መጣህ?» ሲል ጠየቀው። የእግዚአብሔር ሰው ቅዱስ ኢየሱስ ሞዐም «የመጣሁት ለደብረ ዳሞ መነኰሳት እታዘዙለውና አገለግላቸው ዘንድ መሽሔ ለመሆን እና የአቡኾን በረከት ለማግኘት ነው» ሲል ለአባ ዮሐኒ መለሰለት። አባ ዮሐኒም «በታላቅ ድሎትና ምቾት የኖርክ አንተ መሽሔ መሆን ትችላለህን?» አለው።

ኢየሱስ ሞዐም አባ ዮሐኒን በትሕትና እንዲህ አለው፦ «እግዚአብሔር በቸርነቱና በቅዱስ ፈቃዱ ተቀባይነት ባላት በአንተ ጸሎትም ቢረዳኝና ደግሞም አባቶቼ

ቅዱሳንን ያስቻለ አምላኬ በያስችለኝ መነኩሴ እሆናለሁ አለው።» በዚያን ጊዜ አባ ዮሐኒ ኢየሱስ ሞዐ የያዘውን ነገር ተቀብሎ ወደገዳመ ካስገባው በኋላ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐን እስከ ማታ ድረስ ይፈጭ ዘንድ ወደ ወፍጮ ቤት ወሰደው። ከአጋው መነኰሳት ጋርም የመንፈቀ ሌሊት ጸሎትንና ጾምን ሠራለት።

ጠዋት ጠዋት ሲነጋ ይፈጭ ዘንድ ወደ ተግባሩ ይሄዳል። እንዲህ ባለ ግብርም እየተጋ ከወንድሞቹ መነኰሳት ጋር ብዙ ዘመን ኖረ። መምህሩ አባ ዮሐኒም ሰውነቱን መንገድ በመሄድ ያደክም ዘንድ ወደ ገበያ እንዲሄድ አዘዘው። በዚያን ጊዜም መምህሩ አባ ዮሐኒ እንዳዘዘው ለገዳመ ተልእኮ ወደ ሩቅ አገር ሄደ። በመንገድ ላይ እየሄደ ላለም ብዙ ሽፍቶች አገኙትና ስንቁንና ልብሱን ቀምተው ታላቅ ድብደባ ደበደቡት። በዚያም ላይ ወግተው ይገድሉት ዘንድ ጦር ሰበቁበት። የእግዚአብሔር ሰው ቅዱስ ኢየሱስ ሞዐ ግን ሊወጉት ባላቸው ሰዎች ፊት ራሱን አዘንብሎ «ስለ አምላኬ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ግደሉኝ፤ እርሱ ስለ እኔ ተሰቅሎ ሞትን ተቀብሏልና» አላቸው።

እነዚያ ሽፍቶችም አንገቱን ገትቅ አድርጎ ራሱን አዘንብሎ ሲሰጣቸው ባዩት ጊዜ የትዕግሥቱን ብዛት ፈጽመው በማድነቅ ተውት፤ የወሰዱበትን ስንቁንና ልብሱንም ሁሉ መለሱለት። ከወሰዱበትም ያስቀሩበት

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ምንም ነገር የለም። እርሱም በሌላ መንገድ በመሄድ ከሩቅ ሀገር ዘንድ ደረሰ። በዚያም ሳብዙ ጊዜ የገዳሙን ተልእኮ ሲያከናውን ቆይቶ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ገዳሙ ወደ መምህሩ አባ ዮሐኒ ተመለሰ።

ከመምህሩ በደረሰም ጊዜ ሲያከናውን የነበረውንና በተልእኮ የሰበሰበውን ለመምህሩ ለአባ ዮሐኒ አስረከበው። አባ ዮሐኒም ሰውነቱ እንዲያሣርፍ ዳግመኛ ለገዳሙ ተልእኮ ይሄድ ዘንድ አሁንም እንደገና አዘዘው። ከቅዱስ አባ ዮሐኒ ጋር አብረውት የነበሩት ሌሎቹ መነኰሳት ግን ይህን ሰው አባ ኢየሱስ ሞዐን ትንሽ ያርፍ ዘንድ ተወው አሉት። አባ ዮሐኒም ለእነዚያ መነኰሳት እንዲህ አላቸው፦ «መንፈስ ቅዱስ በአፈ ዳዊት አድሮ የተናገረውን ‹በዚህ ዓለም የደከመ ለዘለዓለሙ በሕይወት ይድናል[1]› ያለውን አልሰማችሁምን? በዚህ ዓለም ካረፈ በኋላ በሰማያት ዕረፍትን አያገኝም።» አባታችን ኢየሱስ ሞዐም ይህን ነገር ከመምህሩ ከአባ ዮሐኒ እንደበት በሰማ ጊዜ በታላቅ ደስታና በብዙ ፍላጎት ሆኖ «አባቴ ሆይ አንተ እንደምትሰው ይሁን» አለ። ያን ጊዜም እንደ ልማዱ ወጥቶ ወደ ገበያ ለተልእኮ ሄደ።

በመንገድ ላይ እየሄደ ሳለም ፀሐይ ለመግባት ተቃረበች፤ ፊቱለማም መጣ፤ መሸበት።

1 መዝ. 48፥9

በዚህ ጊዜ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ እጅግ ባለ ጸጋ ወደ ሆነ ወደ አንድ ሰው ያሳድረው ዘንድ ሄደ። ያ ባለ ጸጋ ግን በወንጌል እንደ ተነገረው ክፉ ባለ ጸጋ[2] ያለ ጨካኝ ነበር። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም ያንን ክፉ ባለ ጸጋ ስለ እግዚአብሔር ብለህ በቤትህ አሳድረኝ አለው። ያ ክፉ ባለ ጸጋ ግን ልመናውን አልሰማውም፤ በመልካም አነጋገርም አልተናገረውም፤ ወደ ቤቱም አስገብቶ አላሳደረውም። የእግዚአብሔር ሰው አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ግን በብርድ፤ በረሀብና በጥም በውጭ አደረ። በነጋም ጊዜ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ያንን ባለ ጸጋ «ድሀና ምስኪን የሆንኩ እኔን ለምን ከውርጭ ላይ በውጭ አሳደርከኝ?» አለው።

በልቡናው ርኅራኄ የሚባል ነገር ፈጽሞ የሌለው ጨካኝ የሆነው ያ ባለጸጋ አባታችን ኢየሱስ ሞዐን «አስኪ እግዚአብሔር የሚሰማህ ከሆነ ርገመኝ» አለው። የእግዚአብሔር ሰው አባታችን ኢየሱስ ሞዐም «መርገምን ወደሃታልና ትምጣብህ፤ በረከትን ግን ጠልተሃታልና ከአንተ ትራቅ፤ አለው። ይህንም ብሎ «ከቤትህ በራፍ የተከተለኝን ትቢያ እንኳን አራግፌአለሁ፤ ጌታችን በወንጌል ሌሐዋርያቱ «ከማይቀበሏችሁና ትምህርታችሁን ከማይሰሙ ሁሉ ከዚያች ቤት ወይንም ከዚያች ከተማ ስትወጡ

2 ሉቃ. 16፥9

Scanned by DocumentScanner | Lufick

የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ»[3] ብሎ እንደተናገረ» ብሎ የእሱን ትቢያ አራገፈ። እንዲህ ካደረገ በኋላም አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ወደ ተላከበት ቦታ ሄደ።

በዚያ ክፉና ትዕቢተኛ ባለ ጸጋ ላይ ግን አንድ ኃይለኛ መኮንን ተነሣበት።አቡነ ኢየሱስ ሞዐን የተሳደበውን ያንን ክፉ ባለ ጸጋ በጠላትነት ተዋጋው፣ በጦርም ወጋው። ያ ክፉ ባለ ጸጋም ሞተ። በእንዲህ ያለ ሁኔታ በክፉ አሟሟት ሞተ።መኮንኑም ቤቱን በእሳት አቃጠለው።

አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ከተላከበት ሥራው ሲመለስ የዚያን ትዕቢተኛ ባለ ጸጋ ቤት በእሳት እንደ ተቃጠለ ተመለከተ። የዚያን አገር ሰዎችም «ያ ባለ ጸጋ ወዴት አለ? ወዴትስ ሄደ? ቤቱን በእሳት ተቃጥሉና ጠፍቶ አያለሁና» እያለ ጠየቃቸው። የዚያ አገር ሰዎችም ከእርሱ የሚበረታ አንድ ገገር መጥቶ እንደ ተዋጋውና እንደ ገደለው፣ ቤቱንም እንደምታየው በእሳት አቃጠለው ብለው የሆነውን ነገር ሁሉ ነገሩት። መቃብሩም በመንገድ አጠገብ ነውና ና ተመልከት አሉት።

[3] ማቴ.10:14

አባታችን ኢየሱስ ሞዐም ከዚያች አገር ሰዎች ጋር ሄደ የዚያን ባለ ጸጋ መቃብር አየ። ስለ ደረሰበት መከራና ሞትም አዘነ።

አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ቡተልእኮ ተግባሩ ላይ ሳለ በረሃብና በጥም፣ በብርድና በመራቆት በቀን ሐሩርና በሌሊት ቁር እየተጋደለ በውስጡ ባደረ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰይጣናትን ድል እስኪያደርጋቸው ድረስ ብዙ መከራዎችን ተቀበለ። ሰይጣናትም ሁሉ «ወዴት እንሄዳለን? ወዴትስ እንገባለን? ማደሪያ አሳጥቶናልና፣ ከዚህ ሰው ፊትም የሚወጋን የእሳት ፍላጻ ይወጣልና» ይሉ ነበር።«ይህን ገድለኛና የሥጋ ምኞትን ያሸነፈ የእግዚአብሔር ሰው በሥራው ሁሉ የሚመስለው የለም፣ ፊቱም እንደ ፀሐይ ያበራል» እያሉ ሰይጣናት እንዲህ ይናገሩ ነበር።

ለተልእኮ (ለገዳሙ ሥራዎች) በመሄድና ለመምህሩ በመታዘዝ ፯ (ሰባት) ዓመት ኖረ። ይህ ድካምም በእርሱ ዘንድ ከባድ አልሆነበትም። ይህ የሆነበት ምክንያትም ከእርሱ በፊት የነበሩ ቅዱሳንን ድካማቸውንና ገድላቸውን ስለሚያስብና በሥራውና በሕይወቱ ሁሉ እነርሱን ይመስላቸው ዘንድ ይወድ ስለነበር ነው። የጣፈጠ ምግብን በጨውም ቢሆን፣ እንዲሁም መጠጥንም ቢሆን ፈጽሞ አይቀምስም ነበር።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

እግዚአብሔርም ደካሙንና አገልግሎቱን ያደረጋቸውን መልካም ሥራዎች ሁሉ ወደደለት። ታላቁን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ጾም ሲጾም በሰንበት ካልሆነ በቀር እህል አይቀምስም ነበር፤ ለአክብሮ ሰንበት ትንሽ እህል ወይም ከመሬት አፈር ወስዶ በመቅመስ በቀንና በሌሊት በትጋትና በጸሎት በስግደትና በብዙ ትህርምት ይጾማል እንጂ።

ከዕለታት አንድ ቀን አባቱ አባ ዮሐኒ የእግዚአብሔር ሰው የሆነ አባታችን ኢየሱስ ሞዐን ዘጠኝ ክንድ የሚሆን የዘንባባ እንጨት ያመጣ ዘንድ አዘዘው። ያ ቀንም በዐቢይ ጾም ውስጥ ስለ ነበር አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ከሰንበት በስተቀር ምንም አይቀምስ ስለ ነበር ሰውነቱ ደክሞ የነበረበት ጊዜ ነበር። መምህሩ አባ ዮሐኒ አባታችንን ይህን ያደርግ ዘንድ ያዘዘበት ቀን ሰውነቱ በጾምና በትህርምት የደከመበት ዓርብ ቀን ነበር። እርሱም የመምህሩን ትዕዛዝ በመቀበል ተነሥቶ ወደ ሩቅ ቦታ ሄደ። መምህሩ አባ ዮሐኒ እንዳዘዘው ዘጠኝ ክንድ የሚሆን የዘንባባ ዛፍ ፈልጎ ካገኘ በኋላ ሰውነቱ በትሕርምት ብዛት ደክሞ ስለ ነበር ዘንባባውን ከምድር ማንሣት ተሳነው። በጭንቅ አንሥቶ ተሸክሞ ሲሄድ በመንገድ ላይ ከዐሐዩ መቀትና ከድካም የተነሳ ኃይሉ ደክሞ ነበር። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል ያንን የዘንባባ ዛፍ

ከተራራው ስር ከአደረሰ በኋላ በገመድ አስሮ ተራራውን በማውጣት ወደ መምህሩ ወደ አባ ዮሐኒ ይዞ ደረሰ።

በእንደዚህ ያለ ተጋድሎና ተልእኮ 7 አመት ከኖረ በኋላ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ አባ ዮሐኒን የምንኩስናን ልብስ አልብሰኝ» አለው። ያን ጊዜም የእግዚአብሔር ሰው አባ ዮሐኒ የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐን ተጋድሎውንና ጾሙን ጸሎቱን ፍጹም ትህትናውንና ቅድስናውን ተመልክቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን አስገብቶ ለመነኰሳት እንደሚገባም በላዩ ላይ ጸልዮ፤ ሥርአተ ምንኩስናን አድርሶ የምንኩስናን ልብስ አለበሰው ቆብንም አደረገለት፤ ቅናተ ዮሐንስንም በወገቡ አስታጠቀው። ይህም ቅናተ ዮሐንስ የድንግልናና የንጽሕና ምልክት ነው።

እግዚአብሔርም ድንግልናውንና ትሕትናውን ተመለከተ፤ በሥራው ሁሉም ባረከው፤ የቅዱሳን አባቶች መነኰሳት በረከትም በዙቶ አደረበት። ከማኅበረ መነኰሳትም ውስጥ በእርሱ የሚያገኘን ማንም አልነበረም፤ ሥራው ሁሉ መልካም ነበርና። በልቡም «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ»[4] የሚለውንና የመሳሰለውን ቃለ ወንጌል ሁል ጊዜ ያስብ ነበር።

[4] ማቴ. 5፡16

Scanned by DocumentScanner | Lufick

የቅዱሳንን ዜና ሕይወትና ገድል ሲሰማ ልቡ ይቃጠላል፣ ያለቅሳልም፤ ነገሩንም በልቡ ሰሌዳ ላይ ይጽፈዋል። የሰማዕታትን ዜና ሲሰማም እንዲሁ ያለቅሳል፣ ገድላቸው እስኪፈጸም ድረስም ከማልቀስ ዝም አይልም።

ልቡ ሁል ጊዜ በፍቅረ እግዚአብሔርና እርሱን ባገለገሉት በቅዱሳን ተጋድሎና ጽናት ይቃጠል ነበር። በእኩለ ሌሊት በሚጸልይበት ጊዜ እስኪነጋ ድረስ ከምድር አንድ ክንድ ያህል ከፍ ይል ነበር።

አንድ ቀን እንጨት ሲቆርጥ ሳለ መጥረቢያው ከእጀታው ወልቆ ከአንገቱ ላይ አረፈና ልብሱን ከአንገቱ አንስቶ እስከ ጭኑ ድረስ ቀደደው። የእግዚአብሔር ኃይል ባይጠብቀው ኖሮ እንደ ሁኔታው አደገኛነት ስለቱ አንገቱን በቆረጠውና ነፍሱን ከሥጋው በለየው ነበር። መምህሩ አባ ዮሐኒም ልብሱ እንደተቀደደ ባየ ጊዜ ሰውነቱ የተጎዳ መስሎት ደነገጠ። ሆኖም የእግዚአብሔር ቸርነት ስለጠበቀው ምንም ምን ጉዳት አላገኘውም።

አባታችን አባ ኢየሱስ ሞዐም ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው ዘንድና ያለፉ ታላላቅ አባቶችን በሕይወቱ ይመስላቸው ዘንድ በብቸኝነትና በጽሙና መኖርን ይወዳል። በአላቡ ሁሉ

እግዚአብሔርን የሚያስደስተውን ነገር ያስብ ነበር። የዚህን ዓለም ሕይወትና ተድላ ግን አላሰበም።

ከዕለታት በአንድ ቀን ቅዱስ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ውኃ ያመጣ ዘንድ ትልቅ ማድጋ (እንስራ) ተሸክሞ ወደ ውኃ ጉድጓድ ወርዶ ውኃውን ከቀዳ በኋላ በራሱ ላይ ተሸክሞ ሲሄድ በመንገድ ላይ እግሩን ድንጋይ አደናቀፈው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐ እንደ ቆመ ያ ማድጋ (እንስራ) በድንጋይ ላይ ወደቀ። ሆኖም ማድጋው አልተሰበረም፣ ውኃውም አልፈሰሰም። ከዚያ በኋላ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ወደ ማደሪያው (በአቱ) ገብቶ ብዙ ዘመን በጾምና በጸሎት ተወሰነ። ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ እየመጡ እጅ ይነሡት ነበር። የታመሙትን በእነርሱ ላይና በውኃ ላይ እየጸለየ ይፈውሳቸው ነበር፤ በእርሱ ጸሎት እግዚአብሔር ሕይወትንና ጤንነትን ይሰጣቸው ነበር። ከዚያም ጸሎትንና ጽሙናን በመውደድ በገደል መካከል ብቻውን ሆነ። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም በዚያ ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ወንጌልን ጽፏል። መጽሐፉም በደብረ ዳሞ እስከ ዛሬ ድረስ አለ[5]።

[5] ይህ መጽሐፍ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በደብረ ዳሞ ገዳም ዕቃ ቤት ውስጥ የነበረ ሲሆን ነገር ግን የገዳሙ ዕቃ ቤት

Scanned by DocumentScanner | Lufick

የኢየሱስ ሞዐ መምህርና የደብረ ዳሞ ገዳም አበምኔት የነበረው አባ ዮሐኒ ለሀምሳ ዓመታት ያህል በእሳት የበሰለና የላመ የጣመ እህል አልቀመሰም። ከጾምና ከጸሎት ብዛት የተነሣም ሥጋው አልቆ ቆዳው ብቻ ከአጥንቱ ጋር ተጣብቆ ይታይ ነበር። ይህም አባታችን አባ ዮሐኒ ወደዚህ መንፈሳዊ ሕይወት ከመምጣቱ በፊት ግን ከአገረ ገዥው በታች ሆኖ ታላቅ ባለስልጣን ነበር። በወርቅና በብር በልጽጎ ብዙ ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮች ነበሩት።

ሆኖም ግን ቅዱስ አባ ዮሐኒ ይህ ዓለም ክብሩም ሆነ ደስታው፣ ምቾቱም ሆነ ግዛቱ ማንኛውም ነገሩ ሁሉም እንደ ጥላ ፈጥኖ የሚያልፍ እንደ ሆነ በልቡ አስተዋለ። ከአገረ ገዥው ፊት ቆሞም እንዲህ አለው፦ «እኔ ከአሁን በኋላ የአንተ አገልጋይ አልሆንም! የክርስቶስ አገልጋይ

በ«መብረቅ» ተመትቶ ተቃጠለ በተባለ ጊዜ አብሮ ተቃጥሏል (ጠፍቷል)።

እሆናለሁ እንጂ። በዚህ ጊዜ አገረ ገዥውም «እኔ አብዝቼ ወደድኩህ፣ስልጣንንም ከኔ በታች ሰጠሁህ ስለሆነም አባክህ ከእኔ አትለይ፣ ትተኸኝም አትሂድ» አለው። ቅዱስ አባ ዮሐኒም መልሶ «እኔ ይህን ነገር አስቀድሞ ነግሬህ ነበር፣ አሁንም እኔ የአንተ አገልጋይ አልሆንም» አለው። አገረ ገዥውም ልቡ እንደቆረጠ ባወቀ ጊዜ ተወው። የእግዚአብሔር ሰው ቅዱስ አባ ዮሐኒም ከወርቁና ከብሩ ከከበሩ አልበሳቱም ምንም ምን ሳይዝ ከአገረ ገዥውም ፊት ወጥቶ ደብረ ዳሞ ወደ ተባለው ቦታ ደረሰ። በዚያም በጾምና በጸሎት በስግደትና በትጋት ከዓለም ከወጣ ጆምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በእሳት የበሰለና የላመ የጣመ እህል አልቀመሰም። እንዲህ ሲጋደል ከኖረ በኋላ በሰላም እግዚአብሔር ግንቦት ስምንት ፰ ቀን ዐረፈ፣ ጸሎቱና በረከቱ ከእኛ ጋር ይሁን፣ አሜን።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ምዕራፍ ሦስት:- የሐይቅ ደብረ ነጎድጓድ ቅ/እስጢፋኖስ ገዳም መመሥረት እና የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ወደ ሐይቅ ደሴት መምጣት

የሰማዕታት መጀመሪያ የሆነው የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን የታነፀባት ይህች የሐይቅ ደብረ ነጎድጓድ ደብር ከመመሥረቷ በፊት በውስጥዋ ባሉጥ የሚባል ትልቅ ዛፍ ነበር። ከዛፉ ሥርም ዘንዶ የተባለ አውሬ ይኖር ነበር። ለዚያ ትልቅ ዘንዶ የሚሰግዱና እርሱን የሚያመልኩ ሰዎችም ነበሩ። ለዘንዶውም በዮዝዜው ምግቡን የላም ሥጋ፣ ደምና ወተት ይሰጡት ነበር። ወተቱን የሚጠጣበትም የድንጋይ ገንዳ ነበር።

ያ ገንዳም እስከ ዛሬ ድረስ አለ[6]። ሰዎቹም እንዲያ እያደረጉ ዘንዶውን እየመገቡና እርሱን እያመለኩ ብዙ ዘመናት ኖሩ። ከዚህ በኋላ የመጀመሪያው ጳጳስ አባ ሰላማ ኮሣቴ ብርሃን ጳጳስ ሆኖ ከመጣ በኋላ ሰላማ ዘአዜብ የሚባል ጳጳስ ካልኣ ሰላማ (ሁለተኛው ሰላማ) ወንጌልን እያስተማረ በአዴል(አፋር) ምድር በኩል በመሥራቅ መጣ። ይህ አባት አገሩን እየባረከ እና ወንጌልንም እየሰበከ ደማሞ (ደብረ እግዚአብሔር) የሚባለው ከፍታ ቦታ ደረሰ ከዚያ ሆኖ ይህችን ደሴት ተመልክቶ ወደዳት።

[6] ገንዳው በገዳሙ ቤተ መዘክር ውስጥ ይገኛል፣ ለጎብኝዎችም ክፍት ነው።

የደሴቲቱን ሁኔታ ሲመረምርም ነዋሪዎቿ ለዘንዶ እንደሚሰግዱና እንደሚገብሩ ነገሩት። እርሱም መስቀሉን አንሥቶ በላይዋ ላይ በመስቀል ምልክት የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ባማተበ ጊዜ በፈቃደ እግዚአብሔር ያ ዘንዶ ከዚህ ደረሰ ሳይባል ጠፋ። ከዚህ በኋላ አባ ሰላማ ወደ አክሱም ተመልሶ ለንጉሡ ለዓፄ ድልነዓድ ይችን ደሴት እንዳያትና ልቡ እንደ ወደዳት ነገረው።

ንጉሡንም ይህችን ደሴት መጥቶ ያያት ዘንድ አተጋው። እርሱም በነገሠ በሰባተኛ ዓመተ መንግሥቱ ከጳጳሱ ከአባ ሰላማ ጋር ወደዚች ደሴት መጣ። የመንግሥቱን መናገሻ ከተማም ከአክሱም ወደ ደቡብ ምስራቅ አዛወረ። ያም ንጉሥ መጥቶ ይችን ደሴት ባያት ጊዜ እጅግ ወደዳት፣ ቤተ ክርስቲያን ይሠራባት ዘንድም ወደደ። በዚች ደሴት በስተቀኝ በኩልም ከተማ ሠራ፤ በዚያም ቤተ ክርስቲያን መሥራትን አስቀደመ።

ንጉሡም ቤተ ክርስቲያኑን አሳንፆ በፈጸመ ጊዜ ጳጳሱ በእግዚአብሔር አብ ስም ታቦቱን ቀደሰ፤ ንጉሡም የቤተክርስቲያን ቅዳሴ ቤት አከበረ፤ ታቦቱንም ወደ ቤተ መቅደሱ አስገብቶ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ በፈጸመና ታቦተ ጽዮንን ባስገባ ጊዜ በዓል እንዳደረገ በዓል አደረገ። ያንም ቦታ «ደብረ እግዚአብሔር» ብሎ ሰየመው።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ከዚህ በኋላ በ፰፻፷፪ (862) ዓ.ም በደሴቲቱ ላይ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ጀመረ፤ ይህንም በፈቃደ እግዚአብሔር ፈጸመ። መሠራቷ በተፈጸመ ጊዜም ጳጳሱ አባ ሰላማ በላይዋ ላይ ሜሮንን አፈሰሰባት።

እርሱ ከዚህ አስቀድሞ የእግዚአብሔር መንፈስ በላይዋ ላይ ረቦባት እንዳለ፣ መልአኩ ዑራኤል የጌታን ደም በዕለተ ዓርብ እንደ ቀባት በመንፈስ ቅዱስ አውቋልና። ከዚህ በኋላ ንጉሡና ጳጳሱ ቤተ ክርስቲያኒቱን በማን ስም እንሰይማት? በእመቤታችን በድንግል ማርያም ስም ነው? ወይስ በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል ስም? ወይስ በሌሎች ጻድቃን ሰማዕታት ስም ሲባባሉ ላለ ሥውራን ቅዱሳን ከኢየሩሳሌም የላኩት የሰማዕታት መጀመሪያ የሆነ የቅዱስ እስጢፋኖስንና የቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት የተሸከመች ቶራ (አጋዘን) መጥታ ከባሕሩ ዳር ቆመች። ሕዝቡም ቶራዋን ከባሕሩ ዳር ቆማ ባይዋት ጊዜ ወደ እርሷ ሄዱ ጳጳሱም ታቦቱን ከላይዋ ላይ አወረደ። «ይህ ታቦት ስውራን ቅዱሳን ከኢየሩሳሌም የላኩት የሰማዕታት መጀመሪያ የቅዱስ እስጢፋኖስና የቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት ነው የሚል ጽሑፍም አገኙ። ከዚያም ወደ ደሴቱ ውስጥ አስገቡት። ጳጳሱ አባ ሰላማም ቤተ ክርስቲያኑን አከበረ፤ በሜሮኑም

ሀሰንሀሩናሞን አተማት። ታቦቱንም አስገባ። ንጉሡ አሜ ድልነዓድም ቀያም ብሎ በደብረ አግዘአብሔር እንዳያረገ የትዳሌ ቤቱን በዓል አከበረ። የደሴቷንም ስም «ደብረ ነጎድጓድ» ብሎ ሰየማት። ይህም ቤተ መንግስትና ቤተ ክህነት እንድ ሆነው ሰረት ማለት ነው ። ንጉሡም ከእርሱ ጋር ከነበሉም ካመጣቸው ቱጥራቸው ሦስት ሙዩ የሚሆን ካህናትና ሊቃውንትን ሰራ (መደበ) ። ለቤተ ክርስቲያንም ከነሀር የተሠሩና የነበሩ አልባሳትን የማምኛ መጋረጃዎችን መጽሐፍቶችን ብዙ ቦታምችንም ርስት አድርጎ ሰጠ። ከዚህም በኋላ ሴቶችና ወንዶች ሳይለያዩ ብዙ ዓመታት ተቀመጡ።

በባሕሩ ዳርቻ ዙሪያም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ታነፁ[7]።

---

[7] በሐይቅ በባሕሩ ዙሪያ እስከ ግራኝ መምጣት ድረስ ከአርባ በላይ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ነበሩ የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። ሆኖም በአህመድ ግራኝ ወረራ ወቅት በገዳሙ ውስጥ ካለው ቤተ ክርስቲያን በስተቀር በዙሪያ የነበሩትን ሌሎቹን አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ አያቃጠለ አጥፍቷቸዋል። የአካባቢውን ነዋሪዎችንም እያስገደደ ስላሰለማቸውና በሃይማኖታቸው የጸኑትንም በሰይፍ ስለት ስለ ገደላቸው የፈረሱት ብዙዎቹ በዚያው ጠፍተው ቀርተዋል። ዛሬ ድረስ ቤተ ክርስቲያን የነበረባቸው ብዙዎቹ ቦታዎች ባዶ (ጠፍ) ሆነው የፍርስራሽ ምልክት ይኖባቸዋል። በገዳሙ ውስጥ ያለውን የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ያላፈረሰበት ምክንያት እንዲህ ነው፡- ንጉሡ ልብነ ድንግል በጦርነት የማረከውን የግራኝ ወገን የሚሆን አንድ ሰው በገዳሙ እንዲማርና እንዲጠበቅ ለገዳማውያኑ አደራ ሰጥቷቸው ነበር። ግራኝ እየወረረ ወደዚህ ሲመጣ ያን ሰው አስጠርቶ በገዳሙ ውስጥ አንዴት አንደ ኖረ ጠየቀው። እርሱም ክርስቲያን እንዲሆን ከሚያስተምሩት በስተቀር በመልካም ሁኔታ እየተንከባከቡ ያኖሩት ደግ ሰዎች መሆናቸውን በመግለፅ ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዳያጠፋባቸው ተማጸነው። በዚህ ጊዜ በውስጡ ያለውን ወርቅና ብር ለምጡልኝ ቤተ ክርስቲያችሁን ግን አላቃጥልባችሁም አላቸው። በዚህ ሁኔታ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑና በውስጥ የነበሩት የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ሊቃጠሉና ከውድመት ተረፉ።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ቅ/ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ በመንፈቀ ሌሊት ወደ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ መጣና ጠርቶ እንዲህ አለው፡- «ተነሥተህ ወደ ደብብ ምሥራቅ አገር ሂድ፤ ደብረ ነንድንድ የምትባል ዙሪያዋን በባሕር የታጠረች ቦታ ታገኛለህ፣ ይህችውም ደብረ ሐይቅ ናት፤ ቦታህ እርሷ ናትና ወደዚያ ሂድ።» አለው።

አባታችን ኢየሱስ ሞዐም ተነሥቶ እግዚአብሔርን አመሰገነው። ሲነጋ በማለዳ ወደ አባ ዮሐኒ ሄዶ «አባቴ ቀድሞ ወደ አንተ እንድመጣ የጠራኝ አሁን ደግሞ ከአንተ ተለይቼ ወደ ሌላ ቦታ እንድሄድ አዘዘኝ» ብሎ ነገረው። አባ ዮሐኒም «በደኅና ሂድ፤ የእግዚአብሔር ሰላም ከአንተ ጋር ይሁን የብዙዎች አባት ትሆናለህ » ብሎ በጸሎት አሰናበተው።

ከዚያ በኋላ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ከመንፈሳዊ አባቱ ከአባ ዮሐኒ ቡመለየቱ ዳግመኛም በአካለ ሥጋ እንደማይዋኝ ስላወቀ አለቀሰ። እንዲሁም ከመንፈሳዊ ወንድሞቹ መነኰሳት በመለየቱ በጣም እያዘነ ከደብረ ዳሞ ወጣ። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም ያ የጠራው የእግዚአብሔር መልአክ ቅ/ገብርኤል እየመራው ወደ ሐይቅ መጣ። አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ዙሪአሩ ዳር ከደረሰ በኋላ በዚያ በባሀሩ ዳር የሰፈረው የቅዱስ ጴጥሮስና ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን እየተሳለሙና ቅዳሴ ቀድሶ እያቆረበ ለአድስት ወራት ያህል ኖረ። ከዚያም ስሙ ጌረ አምላክ የተባለው ካህን አገኘውና «ከየት አገር መጣህ?» ብሎ ጠየቀው።

አባታችን ኢየሱስ ሞዐም ከመነሻው አንሥቶ ነገረው። ያ ሰውም ከባሕሩ መሀከል ካለው ደሴት ውስጥ አስገብቶ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እያሟላ በቤቱ አኖረው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም በዚህ በደሴቱ በነበረው የቅዱስ አስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ከቤቱ ስላኖረው ስለ ጌረ አምላክ ፈንታ በትጋት በቅዳሴና በሰዓታት ሲያገለግል የደሴቲቱ ሰዎችም የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐን ትጋቱንና ትሕትናውን ስላዩና በጸጋ እግዚአብሔር የተከለሰና በረድኤተ እምላክ የተጎበኘ እንደ ሆነ ስለተረዱ እርሱ መምህራቸው ሆኖ ይሾምላቸው ዘንድ ወደ ንጉሥ ይትባረክ ወደ ደብረ ሮሃ (ላሊበላ) መልእክተኞችን ላኩ። ንጉሥ ይትባረክም በዚህ ነገር ተስማማ፣ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ሊሐይቅ ቅዱስ አስጢፋኖስ ደብር መምህር ሆኖ ተሾመ።


አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ከደብረ ዳሞ ወደ ደሴቲቷ የመጣው በ፲፪፻፴፬ዓ.ም (1233) ነው። አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ይችን ደሴት ወደዳት። ከደሴቷም ውጭ ላያውጣ በእግዚአብሔር ስም ብፅዓት(ቃል ገባ) አደረገ። ሃያ ዓመትም እንዲህ ከደሴቲቷ ሳይወጣ ተቀመጠ። ከዚህ በኋላ ይኵኖ አምላክ መንግሥት ከያዘ በኋላ ወደ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ መጥቶ ከባሕሩ ዳር ሲደርስ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ከደሴቱ ወጥቶ ወደእሱ ይመጣ ዘንድ ላከበት። አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐም «ከዚህ እንዳልወጣና ከባሕሩ ውጪ የብስ እንዳልረግጥ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ብጽዓት(ቃል ስለገባው) ስላለብኝ ከደሴቷም አልወጣም። ነገር ግን አንተ ወደ እኔ ና» አለው።ንጉሡም «እኔ ወደ ውስጥ ብገባ ደሴቱ አይበቃኝም፣ ሠራዊቱ ብዙ ነውና፤ ነገር ግን አንተ በታንኳ ና፤ ከታንኳው ሳትወርድ እዚያው ላይ እንደሆንህ እንነጋገራለን» አለው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ግን ጎረየነ ክርስቶስና ጒሩተ አምላክ ከሚባሉ ደቀ መዛሙርቶቹ ጋር በጀልባ መጥቶ ንጉሡም በበቅሎ ላይ ሆኖ እስከ ጉልበቱ ድረስ ወደ ባሕሩ ገብቶ ከአባታችን ከኢየሱስ ሞዐ ጋር ተነጋገሩ። አባታችን ኢየሱስ ሞዐ የማለውን መሐላ አስቦ ከታንኳው አልወረደም፣ ወደ ውጭም አልወጣም።

ነገር ግን ከታንኳው ላይ ሆኖ ንጉሡም ከበቅሎ ሣይወርድ አባታችን ኢየሱስ ሞዐን ባርከኝ በጸሎትህም አትርሳኝ አለው። አባታችንም አቡነ ኢየሱስ ሞዐ በረከው። ንጉሡም «የጠየቅኸኝን አፈጽምልህ ዘንድ አደርግልህ ዘንድ የምትፈልገውን የልብህን ምኞት ንገረኝ» አለው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ንጉሡን «ሴቶችን ከዚህ ደሴት እንድታስወጣቸውና ከአንተ ጋር እንድትወስዳቸው፣ ይህችን ደሴት ግን የወንዶች መነኰሳት ገዳም ትሆን ዘንድ አሻለሁ» አለው። ንጉሡም የመምህሩን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐን ቃል በመቀበል በደሴቲቱ ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን ሴቶች እንዲህ አላቸው፦ «እናንተ በዚች ደሴት የምትኖሩ ሴቶች ሁላችሁ ከዚህ ውጡና በእኔ ከተማ ከእኔ ጋር ኑሩ፣ እኔም የምትሹትን ሁሉ እሰጣችኋለሁ፣ አደርግላችኋለሁ። ይህች ደሴት ግን

ለመነኰሳት አባቶች ገዳም ትሆን ዘንድ ይገባል፣ እናንተ ደግሞ ከእኔ ጋር ትኖሩ ዘንድ ይገባል።» ብሎ አዘዘ።



የሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ቤተ ክርስቲያን

በዚህ ምክንያት ሴቶች ከደሴቲቱ ወጡ። ከወጡ በኋላም ከንጉሡ ጋር ወደ እርሱ ከተማ የሄዱ አሉ። ከእርሱ ጋር መሄድ ያልፈለጉት ደግሞ ወደ ሌላ ሀገር የሄዱም አሉ። ሴቶቹ ከደሴቱ ሲወጡ ፀንሳ የነበረችው አንደኛዋ የመውለጃ ጊዜዋ ደርሶ ኖሮ ከባሕሩ ዳር ስትደርስ ምጥ ያዛትና በዚያ ወለደች። ስለዚህም ይህ ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ ‹ምጥ ገበታ› ተብሎ ይጠራል።

ንጉሡም ለአባታችን ለአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ብዙ ቃል ኪዳን ሰጠው። ከእነዚህም መካከል አንዱ ለገዳሙ መገልገያ ይሆን ዘንድ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ መኪንንት የተሰጡትን መተዳደሪያ እርሻዎች ማንም

Scanned by DocumentScanner | Lufick

እንዳይቀማቸው ነው። ሌላውም ቃል ኪዳን ደግሞ ነፍስ የገደለ ወይም ወንጀል የፈጸመ ሰው ወደዚች ደሴት ገብቶ በቤተክርስቲያኑ ቢማጸን ከሞት ፍርድና ከእስራት እንዲድን የሚልና ገዳሙ የመማፀኛ ቦታ እንዲሁም የወንዶች ገዳም እንዲሆኑና ሴቶች እስከመጨረሻ ወደዚህ ገዳም እንዳይገቡ የሚል ነው። ከዚህም ጋር ሴቶች ወደዚህ ገዳም እስከ መጨረሻው እንዳይገቡ[8]

[8] ሴቶች ወደ ገዳሙ እንዳይገቡ የተከለከለው ገዳሙ የአባቶች መነኰሳትና የባሕታውያን የጸሎት ቦታ ስለሆነ መደባለቁ ለመንፈሳዊ ሕይወት ረብህ (ጥቅም) ስለሌለው ነው እንጂ የጽድቅና የኃጢአት ወይም የእድልዎ ጉዳይ አይደለም። ገዳሙ የተመሠረተው ከዓለም ተለይተው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ፈጣሪያቸውን በተከተተ ልቡና ለማገልገል ለሚፈልጉ ሰዎች እንዲሆን እንጂ በአሁኑ ዘመን በአንዳንዶች ዘንድ እንደሚታየው አስተሳሰብ ለጉብኝት (ቱሪዝም) ስላልሆነና በቤተ ክርስቲያችን ትውፊት መሠረት ደግሞ የወንዶችና የሴቶች የጸሎት በኣት የተለያየ በመሆኑ ነው።

ወደ ሴቶች መነኰሳዪያት ገዳምም ወንዶች አይገቡም፣ ወንዶች የሚገቡት በሴቶቹ በራሳቸው ሊከናወን የማይችለውን የቅዳሴ አገልግሎት ለመፈጸም ሲሆን እነዚያውም በመልካም ሕይወታቸው የተመሰከረላቸው አረጋውያን ተመርጠው ነው። በጥንት የግብጽ ገዳማት (በተለይ በቅዱስ ጳኩሚስ ገዳማት) ወደ ሴቶቹ ገዳማት ወንዶች አይገቡም ነበር። ከሴቶቹ ገዳም ሰው ሲሞት እንኳ ሴቶቹ አዘጋጅተው ከገዳማቸው አውጥተው ነበር ለወንዶቹ መንኰሳት የሚያቀብሏቸው። ከዚያ በኋላ

በአባታችን በአቡነ ኢየሱስ ሞዐ በግዘት ጸንቷል ።

ሌላውም ንጉሡ የሰጠው ቃል ኪዳን ማንም የግል ቤት፣ ርስት አለኝ እንዳይል (ጥሪት፤ ቁሪት እንዳይኖር) ቃል ገባለት። በዚህም መሰረት በአንድነት ከሚኖሩት ማኅበረ መነኮሳት ውጪ በገዳሙ በግል እንዳይኖሩ ሥርዓተ ገዳም ተደነገገ። ንጉሡ በበቅሎ ላይ ሆኖ ከባሕሩ ውስጥ ገብቶ ከአባታችን ከኢየሱስ ሞዐ ጋር እየተነጋገሩ ሳለ ከባሕሩ እባብና አለቅት ወጥቶ በንጉሡ በቅሎ እግር ላይ ተጠመጠመ። አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐም ይህንን ሲያዩ በደሴቱና በባህሩ ውስጥ ያሉ እባቦችና አለቅቶች መርዛቸው ይረክስና የማይጎዳ ይሆን

ወንዶቹ ተቀብለው ጸሎተ ፍትሐት አድርሰው ይቀብራሉ።
ይህ ትውፊትና ባህል በሌሎች ምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያናትም ከጥንት ጀምሮ የነበረና ዛሬም ያለ ነው። ለምሳሌ ግሪኮች «ሞንት አቶስ» የተባለ ሴቶች የማይገቡበት በጣም ጥንታዊ የሆነ ታሪካዊና ታላቅ ገዳም አላቸው። ሴቶች ወደ ገዳሙ እንዲገቡ ምዕራባውያን፤ የአውሮፓ ጎብረት ሳይቀር በሴቶች መብት ተቆርቋሪነት ሽፋን ምሥራቃውይ የሆነውን ባህል ለማጥፋት ብዙ ተጽእኖ ለማሳደር ቢሞክሩም ገዳማውያኑ ግን ለማንም ባለ መንበርከክ ትውፊታቸውን ጠብቀው ይዘው ይገኛሉ።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ዘንድ፣ ሰውንም ሆነ እንስሳን እንዳይነክሱ አወገዛቸው።

በዚያን ጊዜ ንጉሡ የደወል ድምፅ ሰማ። አባታችንን «አሁን ስንት ሰዓት ነው?» ይህ የምሰማውስ የደወል ድምፅ ምንድን ነው?» አለው። አባታችንም «ዘጠኝ ሰዓት ነው» ለጸሎት በሰባቱ ጊዜያት እንዲሁም ለተግባረእድ እንዲደወል አድርጊያለሁ አለው ።

ንጉሡም «የዓቃቤ ሰዓት» ሹመት ሰጠሁህ አለው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም «እኔ ከዚች ደሴት አልወጣምና ሹመቱን ለልጄ ለዘኢየሱስ ስጠው» አለው። ልጁ ዘኢየሱስም ዓቃቤ ሰዓት ተባለ። በዚህ ሁኔታ ንጉሡ ይኸኖ አምላክ ለአባታችን የዓቃቤ ሰዓት[9] ሹመትን ሰጠው።

ከዚህ በኃላ ንጉሡ ወደ ከተማው ተመለሰ፤ አባታችንም ወደ ገደሙ ገባ። በዚያም ፶፩ ዓመት በአበምኔትነት ኖረባት። ይኸውም ሃያ ዓመት በንጉሥ ይትባረክና በንጉሥ ነአኩቶ ለአብ ዘመን መንግሥት፤አሥራ አምስት ዓመት በንጉሥ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት፤ ዘጠኝ

[9] የሐይቅ ገዳም መምህራን (አበምኔቶች) የመላረግ ስማቸው ዐቃቤ ሰዓት ነው። የዐቃቤ ሰዓት
ሹመት በዚያን ዘመን ንጉሡ በሚገኝበት የመገኘትና በችሎት የመቀመጥ፤ ፍርድ የመስማትና በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ሃሳቡና ምክሩ የሚጠየቅና የሚደመጥ ነበር። በኋላ ላይ መናነሻው ወደ ጎንደር ሲሄድ ከገዳሙ ጋር ካለው የቦታ ርቀት የተነሣ እንዲሁ ሌሎች ሰዎች«ዐቃቤ ሰዓት» እየተባሉ ስሙን ይይዙ ነበር።

አመት ደግሞ በንጉሥ አግብአ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው።

አባታችንም በሀገራቱ በተለያዩ አትጣጫዎች ተሰማርተው ገዳማትን የመሠረቱና ስብከተ ወንጌልን አስፋፍተው በመስበክ የሰው ልጆች የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ያደረጉ ብዙ ቅዱሳን አባቶችን በቶብና በቅድስና በትምህርት ወለደ።

ከሁሉ በፊት በምድረ ኅል (ጋስጫ አጠገብ) ተቀምጦ መላውን ምድረ አምሐራን ያስተማረው አባ በጸሎተ ሚካኤል በምንኩስና ከአባታችን ከኢየሱስ ሞዐ ተወለደ።

ይህም አባታችን ተክለ ሃይማኖት ከአባታችን ከኢየሱስ ሞዐ በምንኩስና ከመወለዱ በፊት ነው። ከዚህ በኋላም ከምድረ ወግዳ ይዞ እስከ ጎጃም ያስተማሩት አባ ሕዝቅያስና የደብረ ቍዘቱ አባ ገብረ እንድርያስ፤ ከምድረ ዋድላ አንሥቶ እስከ ዳውንት፤ ከበጌምድር እስከ ደምቢያ የሰበከው የደብረ ዳሪቱ ዕጨጌ አሮን፤ የትግራን ምድር ያስተማረ የበለሳው አቡነ ገብረ ናዝራዊ፤ የሳርክን ምድር ይዞ እስከ ጋዝጌ እና መላውን የአለፋን ምድርና የአገውን ምድር ያስተማረው የዳጋው አቡነ ሂሩተ አምላክ፤ ኋላም መላውን የወለቃን ምድር እስከ ሸግላ ድረስ ያስተማረውና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብራት እስኪባል የደረሰው፤ መጽሐፈ ምሥጢርን፤ ኖኅተ ብርሃንን፤ አርጋኖንን፤ የመዓልትና የለሊት ሰዓታትን፤ መዝሙረ ድንግልን፤ የሕማማት ሰላምታን የደረሰው የደብረ ባሕርይው (ጋስጫ) አባ ጊዮርጊስ በምንኩስና ከአባታችን ከኢየሱስ ሞዐ ተወለዱ።

Scanned by DocumentScanner | Lufick



ጻድቁ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ

አባታችን አቡነ ኢያሱስ ሞዐም በገዳሙ ውስጥ ለእግዚአብሔር በፍጹም በመገዛትና ጸምና ጸሎትን አገልግሎትን በማብዛት ሌሊት ከባሀሩ ውስጥ ቆሞ በመጸለይ በብዙ ተጋድሎ ኖረ።

ቅዳሴ በሚቀድስ ጊዜ ፊቱ እንደ ፀሐይ ያበራ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በነበሩት ሁሉ ላይም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያድርባቸው ነበር። ብዙ እንባና ጸጥታም ይሆን ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቆሞ ዋዛ ፈዛዛ ሲጫወቱ ሲያያቸው ዝም ይሉ ዘንድ ይገሥፃቸው ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍትን እየተረጎመ ስለ ክርስቶስ ያስተምራቸዋል። እንደዚህ ባለ ግብር ከደሴታ ከገባ ጀምሮ ሣይወጣ ፺፪ ዓመት ኖረ።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ምዕራፍ አራት

የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ መምጣት

አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ሲኖር ከብዙ ጊዜ በኋላ ተክለ ሃይማኖት የሚባል ደግና የተባረከ የእግዚአብሔር ሰው ከሸዋ አገር መጣ። አባታችን ተክለ ሃይማኖት ወደ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ከመምጣቱ በፊት በመንገድ አንድ መነኰሴ አገኘና ከየት እንደ ሆነ ጠየቀው። ያ መነኰሴም «እኔ የአባ በጸሎተ ሚካኤል ደቀ መዝሙር ነኝ» አለው። አባ ተክለ ሃይማኖትም «ወደ መምህርህ አድርሰኝ» አለውና ወደ አባ በጸሎተ ሚካኤል ወሰደው። በዚያም እያገለገለና ተአምራትን እያደረገ ፲ አመታት ኖረ።

ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ አባታችን ተክለ ሃይማኖትን «ጻድቅ ደግና የእግዚአብሔር ሰው ወደ ሆነው በደሴት ውስጥ ወደሚኖር አባ ኢየሱስ ሞዐ ሂድ» አለው።

የእግዚአብሔር መልአክ እየመራው ከባሕሩ ዳር ደረሰ። በዚያም ባሕሩን የሚሻገርበት ታንኳ ባላገኘ ጊዜ ያ መልአክ በባሕሩ ላይ እየተራመደ ታየው።

እርሱም አብሮት በባሕሩ ላይ እንደየብስ እየተራመደ ተሻገረና ወደ ውስጥ ገብቶ በቤተ ክርስቲያኑ በር ቆመ። ይህ መልአክም አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ወዳለበት አልፎ ሄደና «ስሙ ተክለ ሃይማኖት የሚባል እግዚብሔርን የሚፈራ አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያኑ በር ቆሟልና ተቀበለው፣ ልብሰ ምንኩስናንም እንድታለብሰው (እንድታመነኩሰው) ወደ እዚህ የመጣው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና» አለው። ይህንም ብሎት ያ መልአክ ከእርሱ ዘንድ ተሰወረ።

ያን ጊዜ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱን ጠርቶ «በቤተ ክርስቲያኑ በር እንግዳ አለ ሂድና ተቀብለህ ወደ እኔ ይዘኸው ና» አለው። ያም ደቀ መዝሙር ተቀብሎ ወደ እርሱ አመጣው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ወደ እርሱ ሲመጣ ባየውጊዜ ገና ወደ እርሱ ከመምጣቱ አስቅድሞ የእግዚአብሔር መልአክ ክብሩን ነግሮታልና ከመቀመጫው ተነሣ፣ ከእርሱ ጋርም አስቀመጠው።

አቡነ ኢየሱስ ሞዐንም «አባቴ ሆይ፣ የምንኩስና ልብስ እንድታለብሰኝ መጥቻለሁ» አለው። አቡነ ኢየሱስ ሞዐም ወደ እርሱ ከመምጣቱ በፊት ግብሩን በመንፈስ ቅዱስ አውቆ ነበርና እሺ አለው። በብዙ እርዳታና ተጋድሎ ከቆየ በኋላ የምንኩስናን ልብስ አለበሰው (አመነኰሰው)፣ ቅናትና ቀሚስ ቆብም ከአባታችን

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ከኢየሱስ ሞዐ ተቀበለ። ከመመንኰሱ በፊትም በእርሱም ዘንድ ፯ (ሰባት) ዓመት ተቀመጠ። ከመነኰሰ በኋላ ደግሞ ፫(ሦስት) ዓመት ተቀመጠ።

ከዚህ በኋላ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ትግሬ (ደብረ ዳሞ) እሄዳለሁ አለ። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም አባ ተክለ ሃይማኖትን እንዲህ አለው፦ «የተባረክህና እግዚአብሔር የባረከህ ልጄ ሆይ፣ በሰላም ሂድ፣ የአባቶቼ አምላክ እግዚአብሔር መንገድህን ያቅናልህ።» ከዚያም ሁለቱም ተነሥተው ጸሎትን ጸለዩ፤ አባታችን ኢየሱስ ሞዐም አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ባረከው። ከዚያም አባታችን ኢየሱስ ሞዐ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ይሸኘው ዘንድ ሁለቱም በባሀሩ ላይ እንደ ደረቅ መሬት እየተራመዱ ተጓዙ።

አባታችን ኢየሱስ ሞዐ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን እንዲህ አለው፦ «አባቴን አባ ዮሐኒን እንዲህ በለው፦ ከአንተ ተለይቼ በመጣሁ ጊዜ አስኬማን ከአንተ ዘንድ ሳልቀበል መጣሁ። እዚህም ከደረስኩ በኋላ ጽሙናንና ብቸኝነትን ከመውደዴ የተነሣ በዚች ዙሪያዋን በባሕር ወደ ታጠረች ደሴት ከገባሁ በኃላም ከዚች ደሴት ላልወጣ ብጽዓት ስላደረግሁኝ ወዳንተ እንዳልመጣና የቀረኝን አስኬማ ከእጅህ እንዳልቀበል ይህ ብጽዓት ከለከለኝ። አሁንም

አስኬማን ላክልኝ ብለህ ንገረው። አንተም ለራስህ ከእርሱ ዘንድ አስኬማ ተቀበል፤ ከአስኬማ በስተቀር ከእኔ ዘንድ ያልተቀበልከው የቀረህ የለምና ለእኔም ከአባቴ ከአባ ዮሐኒ እጅ አስኬማ ተቀብለህ አምጣልኝ።»

ይህን ብሎ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ወደ አባ ዮሐኒ ወደ ደብረ ዳሞ ላከው። ከዚያም በእግዚአብሔር ፈቃድ ብፁዕና ቅዱስ ከሆነ ከአባታችን ከተክለ ሃይማኖት ጋር አብረው በመቆየታቸውና በሁኔታው ደስ እያለው ወደ በኣቱ ተመለሰ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖትም አባ ዮሐኒ ካለበት ደብረ ዳሞ ደረሰ። አባ ዮሐኒም አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ባየው ጊዜ እጅግ ደስ አለው፤ ወደደው፣ ሳመውም። እርሱም ከአባታችን ከኢየሱስ ሞዐ ስለ መምጣቱና እርሱ የላከው መሆኑን ነገረው።

«አስኬማን ትሰጠኝ ዘንድ ወዳንተ መጣሁ» አለው። እንዲሁም «ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ወደ ኢየሩሳሌም ልሄድ እወዳለሁ» አለው።

አባ ዮሐኒም «አሁን የምትሄድ አይመስለኝም፤ በዚህ የብዙዎች ወንድሞች መነኰሳት አባት ትሆን ዘንድ አለህ እንጂ። ስምህም በዓለም ሁሉ ይታወቃል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር በመልካም ቦታ ያኖረን ዘንድ አብረን እንኑር አለው።»

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ይህንም ብሎ አስኬማን ሰጠው። በጸሎት ጽሙዳን ሆነው አብረው ኖሩ። አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ከአባ ዮሐኒ ጋር ፲፪ ዓመት ኖረ።

ከዚህም በኋላ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአባ ዮሐኒ የራሱንና የአባታችንን አስኬማ ብቻ ተቀብሎ ወደ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ተመለሰ። ከዚያም አቡነ ኢየሱስ ሞዐ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን፦ «ልጅ ሆይ፣ በደኅና መጣህን?» ብሎ ጠየቀው። እርሱም «በተወደደች ጸሎትህ በደኅና መጣሁ» አለው።

አባታችን ኢየሱስ ሞዐም «ነግሬህ እንደ ነበረው አስኬማን አመጣህልኝ?» አለው። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በትሕትና አንጋገር «አዎ አምጥቼልሃለሁ» አለው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም «ስጠኝ» ባለው ጊዜ አቡነ ተክለ ሃይማኖት «በቀዳሜ ሰማዕት በቅዱስ እስጢፋኖስ መንበር ላይ አስቀምጬዋለሁና በእጅህ አንሥተህ ያመጣሁልህን አስኬማ መላእክት አድርግ» አለው።
አቡነ ኢየሱስ ሞዐም «ሰው ከእግዚአብሔር ካልተሰጠው በስተቀር ጸጋን ለራሱ በራሱ ሊወስድ የሚችል የለምና አንተ ስጠኝ፣ ልጅ ስትሆን አባት ሁነኝ» አለው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ይህን ባለ

ጊዜ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለአቡነ ኢየሱስ ሞዐ አስኬማ መላእክትን ሰጠው።[10]

አባታችን ኢየሱስ ሞዐ በተጋድሎ በገዳሙ ሲኖር አንድ ከእንጨት የተሠራ ወንበር ነበረው። ከዕለታት በአንድ ቀን ያ ወንበር አንድ እግሩ ተሰበረ።

---

[10] እዚህ ላይ አንዳንድ ገድላት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአባ ዮሐኒ ያመጣውና ለአቡነ ኢየሱስ ሞዐ የተሰጠው ቆብን ነው የሚሉት ምናልባት ቆብና አስኬማ አንድ ዓይነት እየመሰላቸው ሊሆን ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ከአባ ዮሐኒ ቆብን (ምንኩስናን) ሳይቀበል አልመጣም። ሳይቀበል የመጣው አስኬማን ነበር። አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አምጣልኝ ብሎ የላከውና አርሱም ያመጣለትም ይህንኑ ሳይቀበል የመጣውን አስኬማን ነው እንጂ ቆብን አይደለም። አስቀድሞ ከአባ ዮሐኒ ሳይመነኩስ መጥቶ ቢሆን ኖሮ አነ አቡነ በጸሎተ ሚካኤልን፣ አቡነ ሕዝቅያስን፣ አቡነ ገብረ አንድርያስን፣ አቡነ አሮንንና ሌሎችንም በምንኩስና መውለድ (ማመንኩስ) ባልቻለ ነበር።
አስኬማ የሚባለው ከምንኩስና በኋላ በተጋድሎ ሕይወታቸው ብዙ መንገድ ለተጓዙ አበው የሚሰጥ ልዩ መዓረግ ነው። አስኬማ የተቀበለ መነኩሰም ሁል ጊዜ በጸሎት ጽሙድ መሆን አለበት፣ ሲደከመው እንደ ተቀመጠ ትንሽ ሽለብታ ማሸለብ ካልሆነ በስተቀር ምንጣፍ አንጥፎ በጎኑ ተጋድሞ አይተኛም፤ ሌላም ብዙ ከፍ ያሉ ሕይዎታዊ መንገዶችን ይከተላል። በአጠቃላይ ሕይወቱ የመላእክትን ሕይወት እንዲመስል የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል። መዓርጉ «አስኬማ መላእክት»የሚባለው ለዚህ ነው።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

አባታችንም ይህን ባየ ጊዜ አዘነ። እንደ ልማድም ወደ ጸሎት ሄዶ ጸሎቱን ጨርሶ ሲመለስ ያ አንድ እግሩ የተሰበረው ወንበር እንደ ቀድሞው ደኅና ሆኖ አገኘው፤ እግዚአብሔርንም አመሰገነው። ያም ወንበር እስከ ዛሬ ድረስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛል። በእጁ እየሰራ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ የመቅረዝ መብራቶችን አደረገ። በበዓለ እግዚአብሔርና በጻድቃንና በሰማዕታት በዓላት መብራቶችን ያበራ ነበር። የእነዚያ መብራቶችም ቁጥራቸው ሃያ አራት ፳፬ ነበር።ሠላሳ መጻሕፍትም ጽፎ ሰጥቷል።

ለቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ እያገለገለ ኖረ። እንዲህ ሲኖር ሳለ ከዚህ በኃላፊው ዓለም የመለየቱን ነገር አስቦ ከሰው ጋር እንዳይነጋገር ወደ በኣቱ ገብቶ ብቻውን በጽሙናና በፀጥታ እግዚአብሔርን በመፍራትና ፈቃዱን ሁሉ በመፈጸም በሥራው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እየረዳው ኖረ። ሰውነቱንም በብዙ ሥራና ገድል

አደከመ፤ የዚችን ዓለም ብዕሏንና(ኃብቷን) ተድላዋን ተስፋ የሚያደርጉ ሰዎች እንደሚሹት መብልና መጠጥ ለሰውነቱ በተጋድሎ ላይ ተጋድሎን ጨመረ። መልካም ሥራ እጅግ አበዛ። እራሱንም ኃጢአተኛ ያደርግ ነበር። "እኔ ትል ነኝ፣ ሰውም አይደለሁም። በሰው ዘንድ የተናቅሁ በሕዝብም ዘንድ የተዋረድሁ ነኝ"[11] ይል ነበር።ዳግመኛም "አምላኬ ሆይ፣ ሁል ጊዜ ከአመፀኞችና ከግፈኞች እጅ አድነኝ። ጌታዬ ሆይ፣ ተስፋዬ አንተ ነህና። ጌታዬ ሆይ ከሕፃንነቴ ጀምሮ ተስፋ አደረግሁህ፣ በእናቴም ማኅፀን በአንተ ጸናሁ፣ በእናቴም ማኅፀን ውስጥ አንተ ጠበቅኸኝ፣ በየጊዜው ሁሉ ትዝታዬ አንተ ነህ" ይል ነበር።

ዳግመኛም "እንደ ይቅርታህ ብዛት መጠን ይቅር በለኝ። እንደ ቸርነትህ ብዛት መጠን ኃጢአቴን አስተሥርይልኝ፣ ከኃጢአቴም ሁሉ አጠበኝ አንጻኝም፣ በደሌን እኔ አውቀዋለሁና[12]" ይላል።ዳግመኛም "ከንፈሮቼ ደስ እያላቸው ለስምህ ምስጋና ያቀርባሉ፣ በመኝታዬም አስብሃለሁ ረዳት ሆነኸኛልና፣ በጥዋት ቸርነትህን እናገራለሁ፣ በክንፈ ረድኤትህም እታመናለሁ፣ ሰውነቴም አንተን ተከተለች[13]" ይላል።

ዳግመኛም "የማያልፈውን ተድላ አገኝ ዘንድ በዚህ በሚያልፈው ዓለም እደክማለሁ፣ በዓለም የደከመ

[11] መዝ 21:4

[12] መዝ 50:1-3

[13] መዝ 63:5

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ሰዘለዓለም ይኖራልና። በዚህ በአንቱው ዓለም ያለው ሁሉ ሀብቱም ንብረቱም ክብሩም ሁሉም አንቱ ነው፤ ሁሉም አንቱ የአንቱ አንቱ ነው የሚለውን የመጽሐፍት ቃል" ይል ነበር። እንዲሁም "ዓለሙ ኃላፊ ነው፤ ደስታውም ኃላፊ ነው፣ ሁሉም ኃላፊ ነው፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል"[14] የሚለውን ዘወትር ያስባል። እንዲሁም ነፍሱን ሁል ጊዜ ‹እንዳይፈረድብሽ አትፍረጂ ይላት ነበር። በሰፈርሽበት መሥፈሪያ ይሰፍሩብሻልና›[15] በማለት ነፍሱን ይህን ሁሉ ምክር ይመክራት ነበር። በየቀኑ በራሱ ላይ ምክርንና ዘለፋን ይጨምራል። "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ በዚያ አንተ አለህ፤ ወደ ጥልቁም ብወርድ ከዚያ አለህ"[16] ይላል።

እንደዚህ ባለ ግብር ራሱን እየገሠፀ ብዙ ዘመን ኖረ። ቤተ ክርስቲያኑ ተዘግቶ እርሱ በዚያ እየጸለየና እያለቀሰ በውስጥ ያድር ነበር።

[14] ዮሐ. 2:17
[15] ማቴ7:1-2
[16] መዝ. 138:7-8

በዚያም በታቦቱ ፊት ቆሞ እስከ ማለዳ ድረስ በትጋት ሲጸልይ ሲያለቅስና ሲማልድ ያድራል። እንደዚህ ባለ ሁኔታ መኖር ከጀመረ አሥራ አንድ ዓመት ሆነው። ትሀርምትን ከያዘ ደግሞ ሃ፪ ዓመት ሆነው። እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ጠጅና ሌላም መጠጥ በአፉ አልገባም። በዚህ ዓለም የኖረም ጠቅላላ ዕድሜው ደግሞ ፹ሀ ዓመት ከ፮ ወር (ሰማንያ ዘጠኝ ዓመት ከስድስት ወር) ነው።

ሰማንያ ዘጠኝ ዓመት ሲኖርም ዓይኖቹ አልፈዘዙም፤ ኃይሉም አልደከመም፤ የቀድሞ ተጋድሎውንም ከእርጅና የተነሣ አልተወም። ልብሱም ቅጥልጥሉ ብዙ የሆነና የተሰፋፋ የቆዳ አጽፍ ነበር። በምንኩስናው ሃምሳ ሁለት ዓመት ሲኖር በጎኑ አልተኛም፤ ለጎኑም ምንም ምንም ምንጣፍ አላደረገም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል "ነፍሱን የሚወዳት ይጣላት፤ ነፍሱን ስለ እኔ የጣለ ያገኛታልና"[17] እንዳለ ዓለምንና ምኞቷን ሁሉ ፈጽሞ ናቀ።

[17] ማቴ 10:39

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ምዕራፍ አምስት
የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ዕረፍት

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ከዚህ ከኃላፊው ዓለም ድካምና ውጣ ውረድ ሁሉ ያሳርፈው ዘንድ ወደደ። በዚህ ጊዜ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ታመመ። ብዙ የሆኑ መነኰሳት ልጆቹም "የልባችንን አሳብና ምኞት የምታውቅልንና የምታደርግልን ብርሃናችንና መሪያችን አባታችን ሆይ፣ ምን አገኘህ?" አሉት። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም «ሰውነቴ ይደክማል፣ ሕማም ግን የለብኝምና አትደንግጡ» አላቸው። መነኰሳት ልጆቹም «ትንሽ በጎንህ ተኛ» አሉት። የእግዚአብሔር ሰው አባታችን ኢየሱስ ሞዐም "ለሃምሳ ሁለት ዓመት በጎኔ ያልተኛሁትን ዛሬ እንዴት አደርገዋልሁ?" አላቸው። መነኰሳቱም አባታችን ኢየሱስ ሞዐን፣ አባታችን ሆይ፡- "በረከትህን ስጠን፣ የአባት በረከት በልጆች ላይ ጽኑ ነውና" አሉት። ከዚህ በኋላ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ልጆቹን እንዲህ አላቸው፡- "እግዚአብሔር ሁላችሁንም ከታናናሾቻችሁ እስከ ታላላቆቻችሁ ድረስ ይባርካችሁ፣ በረከቱንም ያሳድርባችሁ። እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ፣ እርስ በርሳችሁ ብትፋቀሩ ጠላቶቻችሁ አይችሏችሁም፣ የሚበረታባችሁም አይኖርም። ሰይጣንም ፈጽሞ

ድል አያደርጋችሁም። ፍቅር ሰውን ከክፉ ሥራው ሁሉ እንደሚጠብቀውና ኀጢአትንም እንደሚያመሰስ እወቁ፣ አስተውሉም። እግዚአብሔር ከእናንተ በፊት የነበሩ ቅዱሳንን እንደ ባረካቸው እናንተንም ይባርካችሁ። የሰራችሁትን በደል እግዚአብሔር በቸርነቱና በይቅርታው ይቅር ብሎ ሕይወታችሁን ያማረና እርሱን ደስ የሚያሰኝ ያድርግላችሁ፣ እስከ መጨረሻ ዘመናችሁ እግዚአብሔር በረዳትነት ኃይሉ ከሰይጣን ፈተና ይጠብቃችሁ።

መነኰሳት ልጆቹም ይህን ቃል ብፁዕና ቅዱስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሰው ከአባታቸው ከአቡነ ኢየሱስ ሞዐ አንደበት በሰሙ ጊዜ ሁሉም ከእግሩ በታች ወደቁ፤ አባታቸው ከእነርሱ ሊለያቸው በመሆኑም አዘኑ፣ አለቀሱም። "አባታችን ሆይ፣ ወዴት ትሄዳለህ? እረኛ እንደ ሌላቸውና ተኩላ እንዳገኘ እንደሚነጥቃቸው በጎች እንዳንሆን እንፈራለንና" እያሉ ከእነርሱ ሊለይ ስለ መሆኑ እያዘኑ ተናገሩት። እርሱም አትፍሩ፣ አትደንግጡም፤ በዚህ ዓለም ሕይወት ሳለሁ ያልተወኝ እግዚአብሔር በፊቱ ስቆም እንዴት ይተወኛል? እናንተን የዋሃን በጵጵኝም ለክፉዎች አራዊት አይሰጥኝም፤ እግዚአብሔር በአጥንቶቼ መልካም ሥራውን እንደሚሠራ እኔ አውቃለሁና› አላቸው።

በቀዳሜ ሰማዕት በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ያሉትንም መነኰሳት እንዲህ ሲል ባረካቸው፡-

Scanned by DocumentScanner | Lufick

"ያዕቆብ ልጆቹን እንደ ባረካቸው ከታናናሾቻችሁ እስከ ታላላቆቻችሁ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ደነግጣችሁ በሠራችሁት ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት አይለያችሁ በረከቱን ያብዛላችሁ፤ በውጭና በውስጥ የተባረካችሁ ሁኑ፤ በሥራችሁና በእጃችሁ የያዛችሁት ሁሉ የተባረከ ይሁን፤ በምትዉጡበትና በምትገቡበት በድካማችሁ ሁሉ የተባረካችሁ ሁኑ፤ መሐሪና ቸር የሆነ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ምህረቱን አያርቅባችሁ፤ ይቅርም ይበላችሁ፤ በማህጸር በምትኖሩባት በዚች ገዳም ረሀብና ጥም (ጽምዕ) አይግባ።" በተለይ "ወደ ማኅበራችሁ ረሀብና ጽምዕ አይግባ" ብሎ ባረካቸው። ይህንም ያለበት ምክንያት ከዚህ በፊት በአንድ ወቅት አንድ ሕፃን ከረሀብ ጽናት የተነሣ ምርር ብሎ ሲያለቅስ ባየው ጊዜ ያኔ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ተነሥቶ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲልጸለየ፡- "እስራኤልን በምድረ በዳ ዓርባ ዓመት መጠኑ ድንብላል የሚያህል ጣፋጭ መናን የመገብክበትውና ያጠገብክበትው፤ ነቢዩ ኤልያስንም በቁራ አፍ የሚመስለው የሌለ ሥጋን ስትመግበው የኖርህ፤ በኋላም ወንጌል እንደ ተናገረ ሕዝቡ በተራቡ ጊዜ በአምስት እንጀራ እና በሁለት ዓሣ አምስት ሺህ ሰዎችን መገብህ እንዲተርፋቸው ያደረግህ፤ ሐዋርያትህንም በተራቡ ጊዜ እንደዚሁ ያጠገብሃቸውን አንተ ነህ" እያለ ሌሉችን ብዙ ጸሎታትንም ከጸለየ በኋላ ገሥገሠ አለ።

ከዚያም በኋላ ከሰማይ እንዲህ የሚል ቃል ሰማ፡- "ወዳጄና አገልጋዬ ኢየሱስ ሞዐ ሆይ፤ በገዳምህና ስምህ በሚጠራበት ቦታ ረሀብና ጽመዕ አይሁን፤ ችግርና ጸብ ክርክር በልጆችህ መካከል አይገባም ፤ በውስጥዋም የአህል በረከት አይታጣም እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ መነኮሳት አይታጡባት፤ ሰላሜና በረከቴ ሁል ጊዜ በእዚች ቦታ ይኖራል። የኢየሱስ ሞዐ አምላክ ሆይ፤ ከረሀብና ከችግር አድነኝ፤ ምግቤንና ልብሴን ስጠኝ ብሎ የሚለምነኝንም ልመናውን እሰማለታለሁ፤ ሲሳዩንና ልብሱን እሰጠዋለሁ።" ይህም የበረከት ቃል በዚህ ገዳም እስከ ዛሬ ድረስ አለ።

ዳግመኛም ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባታችን ኢየሱስ ሞዐን "ስምህን የሚጠራና መታሰቢያህን የሚያደርግ፤ በጸሎትህ በአማላጅነትህ የሚማጸን፤ በቦታህ ላይ መልካም የሚያደርግ በገዳምህም ውስጥ የሚቀበር፤ ከሰማያዊ አባቴ ዘንድ ዋጋውን ያገኛል፤ እስከ ፮ ትውልድ እምረዋለሁ፤ ማደሪያውም በተድላ ገነት ከአንተ ጋር ይሆናል" አለው። ከዚህ በኋላ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ከዚህ ከኃላፊው ዓለም የሚያርፉበት ጊዜ እንደደረሰና ከእነርሱ እንደሚለይ በሰሙ ጊዜ ንጉሡ መኳንንቱ ካህናቱም ይባርካቸው ዘንድ በረከትን ለመቀበል ወደ እርሱ መጡ። ከእርሱም ዘንድ ተባረኩ። ንጉሡና መኳንንቱ፤ ካህናቱና ሕዝቡ ሁሉም እስከ ዛሬ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ድረስ በተቀደሰች ጸሎትህ ስትረዳን ነበር እያሉ አለቀሱ። እርሱም "አትፍሩ በልባችሁም አትደንግጡ፣ ነዳይ የሆንኩ እኔን በዚህ ዓለም ሕይወት ያልተወኝ መሐሪው የሰማይና የምድር አምላክ አይተወኝም" አላቸው። እነርሱም በአካለ ሥጋ ሊለያቸውና ከእነርሱ ሊወሰድባቸው በመሆኑ እጅግ አዘኑ አለቀሱም።

እርሱም ባረካቸው፣ እንዲህ ሲል፦ "እግዚአብሔር ሕይወታችሁን ያሳምርላችሁ፣ ምሕረቱንም በላያችሁ ያሳድርባችሁ፣ አምልኰቱንና ስሙን መፍራትን ያሳድርባችሁ ፣ የሃይማኖት ጽንዓትን ይስጣችሁ፤ ከንጉሣችሁ ጋር በሩቅና በቅርብ ካሉ ወገኖቻችሁ ሁሉ ጋር ሰላምን ይስጣችሁ፤ በሰማያዊያንና በምድራዊያን ፊት ሞገስን ይስጣችሁ፣ እግዚአብሔር የምድራችሁን ፍሬ ይባርክላችሁ። በእርሻችሁ ውስጥ እሾህና አሜኬላ አይብቀል፣ በሀገራችሁ አመዳይና ዋግ አይውረድ፣ በቤታችሁም ጠብና ሁከት አይሁን፤ ሁከትና ብጥብጥ ወደ ቤታችሁ አይግባ። ዋዛ ፈዛዛና ከንቱ ነገርን የሚናገር ሰው ወደ ማኅበራችሁ አይምጣ። እግዚአብሔር የደስታና የሐሤት፣ ከጣዕሙ ብዛት የተነሣ ፈጽሞ አጥንትን የሚያለመልም የሕፃናትንና የመላእክትን የምስጋና ቃል ያሰማችሁ፣ ሊቀ ካህናት ጌታችን መድኀኒታችን

ኢየሱስ ክርስቶስ ካለበት ወደ መንግስተ ሰማያት ያግባችሁ አሜን።" እነርሱም ይህን ቡራኬ ከአባታችን ከኢየሱስ ሞዐ ተቀብለው በሰላም ወደ የቤታቸው ሄዱ። ያን ጊዜ ማህበረ መነኰሳቱ ከመነኰላቸው ሊለያቸው የመሆኑን ነገር ሲመለከቱ ሁሉም አለቀሱ። "ለማንስ ትተኸን ትሄዳለህ? እንደ አንተ ያለ አባትስ በየት እናገኛለን?" አሉት። እርሱም "ይህን ማለትስ አይገባችሁም፣ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥም" አላቸው። ይህንንም ብሎ ልቦናቸውን ከኃዘናቸው አጽናናቸው። ከዚህ በኋላ በእርሱ ምትክ ጠባቂ መካሪ አባት እንዲሰጣቸው አባታችንን አቡነ ኢየሱስ ሞዐን ጠየቁት። በዚች ገዳም ውስጥ ያደገውን ተክለ ኢየሱስ የተባለውን በእርሱ ቦታ ለመነኰሳቱ አባት ይሆን ዘንድ ሰጣቸው (ሾመላቸው)። መነኰሳቱንም ሁሉንም ታናናሾቹንና ታላላቆቹንም እንዲተጉና በማንኛውም ጊዜ ለእግዚአብሔር መገዛትን ችላ እንዳይሉ አደራ አላቸው። ደብረ ነጎድጓድ የተባለች ገዳሙንም ባረካት በፈጣሪም አስባረካት። ይህቺን ደሴት (ገዳሙን) የተላያዩ አባቶች ሰዩት ጊዜ አስዘርጋዋታል። እነዚህም፦

፩. አንደኛው ከሁሉ በፊት ጳጳሱ አባ ሰላማ ዘአዜብ (ካልዕ) በደሴቷ ላይ የዘንዶን አምልኮ አጥፍቶ አስባርኳታል።

፪. ሁለተኛውም ከእርሱ በኃላ በመጣው በጳጳስ አባ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ብንያሚን እጅ የተባረከችው መባረክ ነው። እርሱም በሚጸልይበትና ቅዳሴን በሚቀድስ ጊዜ ከዚህ ዓለም አኗኗሩ ይለወጥና ከመላእክት ጋር ፊት ለፊት ይተያይ ነበር።

፫. ሦስተኛም በሠለስቱ አኃው (በሦስቱ ወንድሞች) እጅ ተባረከች። እነርሱም ወንጌልን እያነበቡ ሲተረጉሙና ሲያመሰጥሩ፣ ደቀ መዝሙራቸውንም የጸም መግቢያ ምግባቸውን ሲያዘጋጅ አርባው ቀን እንደ አንድ ቀን ሆኖ ሳያውቁት አለፈ። የሆሳዕና ሌሊት ነጋሪት ተሰማ፤ በዚህም ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፣ ለእግዚአብሔር በሰማያት ምስጋና ይገባል አሉ።

፬. አራተኛ ሃምሳ ሁለት ዓመት በሳኑ ባልተኛው በብፁዕ አባታችን በአቡነ ኢየሱስ ሞዐ እጅ ተባረከች። በባሕሩ ማዶ የነበሩት ከበኣቱ በሌሊት ወጥቶ በባሕሩ ውስጥ ቆሞ ለመጸለይ ወደ ባሕሩ ሲሄድ ያዩታል፤ ገጹ ብሩህ ሆኖ ያበራ ስለ ነበር ክርቱት ይታይ ነበርና። ባሕሩም በውስጡ ቁሞ ባደረገው በጸሎቱ ተቀደሰ።

፭. አምስተኛው ቡራኬ የጻድቃንንና የኃጥአንን ማደሪያ ያይ ዘንድ መላእክት ወደ ሰማይ በወሰዱት በአባታችን በአባ በግዑ የተባረከችው መባረክ ነው።

፮. ስድስተኛ ደግሞ በውስጥዋ ሳለ መላእክት ወደ ሰማይ ባወጡትና ከሀያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ጋር መንበረ ጸባዖትን ባጠነ ጊዜ በአባታችን በአቡነ ተክለ

ሃይማኖት እጅ የተባረከችው ቡራኬ ነው።

፯. ሰባተኛው ቡራኬ በዓታቤ ሰዓት አባ ሠረቀ ብርሃን ነው። እርሱም ማራዋንና ቀኝን ፊታንና ኋላዋን ባረካት።



እንደ መሶብ አንስተው ደሴቷን ሰባት ጊዜ ያስባረኩ ዘጠኙ ቅዱሳን አባቶች።

ከዚህ በኃላ በሦስት ሰዓት ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሄዱና መሥዋዕተ ቊርባንን እንዲያዘጋጁ አዘዞቸው። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም የሕሊናውን ምኞት ይፈጽምለት ዘንድ እንደ ልማዱ ወደ እግዚአብሔር ለመማለድ ለጸሎት ቆመ። ቊርባኑም ከፈጸመ በኃላ ወደ እርሱ መጡ። እርሱንም በጸሎት

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ላይ ሆኖ አገኙት። እነርሱም አደነቁ። አባታችን ኢየሱስ ሞዐም በበአቱ ተኝቶ አደረ። የነፍሱ ከሥጋው መለየት በቀረበ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ በዚያች ሌሊትም እስኪነጋ ድረስ የተኛ አንድም ሰው የለም። ጠዋት ፀሐይ በወጣች ጊዜ ነፍሱ ወጣች፣ በሰላመ እግዚአብሐር በሰንበት ክርስቲያን በ፲፪፻፹፮ (በ1286) ዓ.ም ኅዳር ፳፯ ቀን ዐረፈ። ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።

አባታችን ኢየሱስ ሞዐ ባረፈ ጊዜ ካህናቱና መነኮሳቱ በሥጋው ፊት ሰግደው እጅ ነሡት። እጅ ሲነሡትም ገጹ እንደ ፀሐይ ሲያበራ አዩት። እንደሚገባም በፍየል ሌጦ ገነዙት። በዚያም ታላቅ መጨነቅ ሆነ፣ ሥጋውን ወደ ቤተ ክርስቲያን መውሰድ አቃታቸው። በታላቅ ክብርና ምስጋና ቀበሩት። መታሰቢያውንም አደረጉ።


የአባታችን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ሀብተ በረከቱ፣ ጸሎቱና አማላጅነቱ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ለይኩን ለይኩን

ከዚህ በፊት በገዳመ የታተመ የገዳመን ታሪክ የያዙ መጻህፍትና በራሪ ወረቀቶች ዓመተ ምህረታቸው በዚህ መጽሐፍት መሠረት ታርሞ ይነበብ ዘንድ ስንገልጽ ባታላቅ ትህትናና አክብሮት ነው።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ
ቤተክርስቲያን



ዋጋ ብር 20.00

ከኑ ማሞሚያ ቤት
0930-097938

Scanned by DocumentScanner | Lirick